# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ዓርብ

83ኛ ዓመት ቁጥር 137 ጥር 17 ቀን 2016 ዓ.ም ዋጋ 10:00 ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!



ፀደይ ባንክ (አ.ማ)
TSEDEY BANK (S.C)

የሁሉም ባንክ
Bank for all !

የብዙዎችን ተስፋ ያለመለመ !

በፋይናንስ አቅርቦት በተግባር የተፈተነ እንዲሁም ሰፊና ጽኑ መሰረት ያለው ባንክ በአነስተኛ የፋይናንስ አገልግሎት ዘርፍ በአገለገለባቸው 25 ዓመታት አለም አቀፍ ዕውቅናዎችን ሲያገኝ የቆየው አማራ ብድርና ቁጠባ ተቋም ወደ ፀደይ ባንክ ተሸጋግሮ የተሟላ አገልግሎት በመስጠት ላይ ይገኛል።

Tel: +251 115 58 12 70/011 551 73 48/011 558 99 98
P.O.Box: 9630
E-mail: mekonnenyelewemwessen@tsedeybank-sc.com
Web: www.tsedeybank.org.et
Addis Ababa, Ethiopia


# ከጥር እስከ መጋቢት 6 ነጥብ 6 ሚሊዮን ዜጎች አስቸኳይ ሰብዓዊ ድጋፍ ያስፈልጋቸዋል

## - ለድጋፉ 9 ነጥብ 2 ቢሊዮን ብር ያስፈልጋል

**ፋንታነሽ ክንዴ**

አዲስ አበባ፡- ከጥር እስከ መጋቢት ወር 2016 ዓ.ም ድረስ 6 ነጥብ 6 ሚሊዮን ወገኖች የአስቸኳይ ጊዜ ዕለት ደራሽ ዕርዳታ እንደሚያስፈልጋቸው የኢፌዴሪ የመንግሥት ኮሙኒኬሽን አገልግሎት አስታወቀ።

የመንግሥት ኮሙኒኬሽን አገልግሎት ሚኒስትር ዴኤታ ሠላማዊት ካሣ ትናንት በሰጡት መግለጫ እንዳሉት፤ መንግሥት አጋር አካላት ጋር በመተባበር በድርቅ፣ በግጭትና በሌሎችም ምክንያቶች አስቸኳይ ድጋፍ ለሚያስፈልጋቸው ዜጎች ድጋፍ ሲያቀርብ ቆይቷል። ከጥር እስከ መጋቢት ወር 2016 ዓ.ም ድረስ 6 ነጥብ 6 ሚሊዮን ወገኖች አስቸኳይ የእለት ደራሽ ዕርዳታ ያስፈልጋቸዋል። ለዚህ ምላሽ ለመስጠትም 9 ነጥብ 2 ቢሊዮን ብር ያስፈልጋል።

ምላሹ በመንግሥትና አጋር አካላት የጋራ ቅንጅት የሚከናወን መሆኑን ጠቅሰው፤ የፌደራል መንግሥት በኢትዮጵያ አደጋ ስጋት አመራር ኮሚሽን አማካኝነት ከጥር ወር 2016 እስከ የካቲት ወር 2016 ዓ.ም ለሚኖረው ምላሽ 500 ሺህ ኩንታል ስንዴ በመመደብ የቅድሚያ ቅድሚያ ምላሽ ለሚሹ ከ3 ነጥብ 3 ሚሊዮን በላይ ወገኖች ተደራሽ እንደሚደረግ ገልጸዋል። ቀሪውን ፍላጎት በአጋር አካላት እንደሚሸፈን ታሳቢ ተደርጎ እየተሠራ ነው ብለዋል።

አስቸኳይ ድጋፍ ከሚያስፈልጋቸው አጠቃላይ ዜጎች ውስጥ 4 ሚሊዮኑ በአፋር፣ ትግራይና አማራ ክልሎች

ከጥር እስከ መጋቢት ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል



ፎቶ፡ ዳኜ አበራ

የመንግሥት ኮሙኒኬሽን አገልግሎት ሚኒስትር ዴኤታ ሠላማዊት ካሣ






## ታጣቂዎች ጠብመንጃቸውን በማስቀመጥ ሕዝቡን ከቀውስ ለማውጣት እንዲጥሩ ኢዜማ ጥሪ አቀረበ

### - ለረሀብ የተጋለጡ ዜጎችን ለመታደግ አፋጣኝ መፍትሔ ሊወሰድ ይገባል

ገጽ 4



## “በቀጣናው በጋራ ለመልማት ፍላጎት ካለው ሀገር ጋር ኢትዮጵያ ለመወያየት ዝግጁ ናት”

### - አምባሳደር መለስ ዓለም (ዶ/ር) የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ቃል አቀባይ

**ሞገስ ጸጋዬ**

አዲስ አበባ፡- በቀጣናው በጋራ ለመልማት ፍላጎት ካለው ሀገር ጋር ኢትዮጵያ ለመወያየትና ለመደራደር ዝግጁ ናት ሲሉ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ቃል አቀባይ አምባሳደር መለስ ዓለም (ዶ/ር) አስታወቁ።

የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ቃል አቀባይ አምባሳደር

“በቀጣናው በጋራ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል

# ለሀገራዊ ምክክሩ ስኬታማነት ምሑራን ጉልህ ሚና መጫወት አለባቸው

**መዓዛ ማሞ**

አዲስ አበባ፡ ለሀገራዊ ምክክሩ ስኬታማነት ምሑራን ጉልህ ሚና መጫወት እንዳለባቸው ሀገራዊ የምክክር ኮሚሽን አስታወቀ።

አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ከሀገራዊ ምክክር ኮሚሽን ጋር በመተባበር “ለሀገራዊ ምክክርና መግባባት የምሑራን አበርክቶ” በሚል ያዘጋጀው ልዩ ጥናታዊ ሴሚናር ትናንት ተካሂዷል።

በውይይቱ ላይ የተገኙት የኮሚሽኑ ምክትል ዋና ኮሚሽነር ሂሩት ገብረሥላሴ እንደተናገሩት፤ መሠረታዊ የሀሳብ ልዩነቶች ከሚስተዋልባቸው የኅብረተሰብ ክፍሎች መካከል ምሑራን ዋንኞቹ ናቸው። ከዚህ አኳያ የሀሳብ ልዩነቶችን በውይይት ለመፍታት በሚደረገው ሀገራዊ ምክክር ስኬታማነት ምሑራኑ ጉልህ ሚና መጫወት አለባቸው።

በምክክሩ ሂደት ላቅ ያለ ተሳትፎ ከሚኖራቸው የኅብረተሰብ ክፍሎች መካከል ምሑራን እንደሚጠቀሱ አመልክተው፤ መሠረታዊ የሀሳብ ልዩነቶችን ያመጡ

ለሀገራዊ ምክክሩ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል











ወይዘሮ ነፊሳ አልመሐዲ

# ጥበበኞችን በሕይወት እያሉ ለማመስገን የሚያስችል እውቅና ሊሰጥ ነው

ዳግማዊት ግርማ

አዲስ አበባ፡- ጥበበኞችን በሕይወት እያሉ የማመስገን ባሕልን ሊያበረታታ የሚያስችል የእውቅና መርሐግብር ሊከናወን መሆኑን የባሕልና ስፖርት ሚኒስቴር ገለጸ።

ጥር 22 የሚከናወነውን 3ኛው "ክብር ለጥበብ" የእውቅና አሰጣጥ መርሐግብር በሚመለከት ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ ትናንት ለጋዜጠኞች መግለጫ ሰጥቷል።

መግለጫውን የሰጡት በሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ የኪነጥበብ ሥነጥበብና ፈጠራ ልማት ዘርፍ ዴኤታዋ ወይዘሮ ነፊሳ አልመሐዲ እንዳሉት እውቅና አሰጣጡ እስከዛሬ ሲኬድበት የኖረውን ሰው ከሞተ በኋላ የማሞገስ ልምድ የሚያስቀር ነው።

እንደ ወይዘሮ ነፊሳ ንግግር፤ ጥበበኞች በሕይወት እያሉ ኢትዮጵያ ታመሰግናችኋለች ለማለት በማሰብ በየዓመቱ የሚከናወነው የክብር ለጥበብ የእውቅና አሰጣጥ ላይ 50 አካላት እውቅና ይሰጣቸዋል።

በ"ክብር ለጥበብ" የእውቅና አሰጣጥ በሀገራችን የጥበብ ዘርፍ ላይ የራሳቸውን አሻራ ያበረከቱ እና አሁንም እያበረከቱ ለሚገኙ ባለሙያዎች በ12 ዘርፍ ላሉ 50 የኪነጥበብና እደጥበብ ሙያተኞች የሚሰጥ ይሆናል።

ወይዘሮ ነፊሳ የኪነ-ጥበብ ሥነ-ጥበብበና ዕደ-ጥበብ ዘርፍ ባለሙያዎች ለሀገራቸው ኢትዮጵያ ላበረከቱት አስተዋፅዖ የሚሰጥ ሀገር አቀፍ የእውቅና መርሐ-ግብር እንደሆነ ገልጸዋል።

ሚኒስትሯ እንደገለጹት የባሕልና ስፖርት ሚኒስቴር በአዋጅ ከተቋቋመበት እና ከተሰጠው ተግባርና ኃላፊነት ውስጥ አንዱ እና ዋነኛው የኪነ-ጥበብ የሥነ-ጥበብና የዕደ-ጥበብ ዘርፉን ተልዕኮ ለማስፈጸም ስለመሆኑ አመልክተዋል ።

የመሥሪያ ቤቱን ተልዕኮ በማስፈጸምና በማበረታታት በጥበብ ዘርፉ ላይ የሚሠሩ ሙያተኞችን ማበረታታት እና እውቅና መስጠት አንዱ የተልዕኮ አካል በመሆኑ ይህ መርሐ-ግብር ተዘጋጅቷል ሲሉ አብራርተዋል።

በእውቅና መርሐ ግብሩ በቴአትር፣ በፋሽን፣ በሙዚቃ እንዲሁም ዲጄን ጨምሮ በአስራ ሁለት ዘርፎች ለ50 ሙያተኞች እውቅና የሚሰጣቸው ሲሆን በሽልማት መርሐ ግብሩ ወጣት እና አንጋፋ የጥበብ ባለሙያዎች ይሳተፉበታል ተብሏል።

በ2013 ዓመተ ምሕረት የተካሄደው የመጀመሪያው የእውቅናና ሽልማት መርሐ-ግብር በውድድር መልክ ሲካሄድ እንደነበርና ከ2ኛው ክብር ለጥበብ የእውቅና መርሐ ግብር ጀምሮ ዝግጅቱ የውድድር መርሐ -ግብር ሳይሆን እውቅና ለመስጠት ያለመ መርሐ ግብር እንደሆነ በመድረኩ ተመላክቷል።

# የቀድሞ ተዋጊዎችን ወደሥራ ለማስገባት የንግዱ ማኅበረሰብ ሚና ወሳኝ ነው

ሔርሞን ፍቃዱ

አዲስ አበባ፡- የቀድሞ ተዋጊዎችን ወደ ሥራ ለማስገባትና ሠላማዊ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ ለማዳበር የንግድ ማኅበረሰቡ ሚና ወሳኝነት እንዳለው ተገለጸ። የኢትዮጵያ ንግድ ማኅበራት ዘርፍ ምክር ቤት ከሀገራዊ ተሐድሶ ኮሚሽን ጋር በመተባበር ከንግዱ ማኅበረሰብ ጋር ትናንት ውይይት አካሂዷል።

በውይይቱ ወቅት የተሐድሶ ኮሚሽን ኮሚሽነር አምባሳደር ተሾመ ቶጋ እንዳሉት፤ የቀድሞ ተዋጊዎችን ወደ ሥራ ለማስገባት ከንግዱ ማኅበረሰብ ጋር የተደረሰው ስምምነት የዝግጅት ሥራዎች በጥሩ ሁኔታ እየተፈፀመ ነው። ይህ ደግሞ ሠላማዊ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ እንዲፈጠር ያስችላል።

የልማት ሥራዎችን ለማከናወን ሰላምን ማስፈን እንደሚያስፈልግ የጠቀሱት አምባሳደር ተሾመ፤ በተለይ የቀድሞ ተዋጊዎች እንደ ማኅበረሰብ ወደ ልማትና ወደ ሥራ እንዲገቡ፤ እንዲሁም ሠላማዊ እና ውጤታማ ሕይወት እንዲኖሩ የሚያስችል ሥራ ለመሥራት ስትራቴጂ መያዙን አመልክተዋል።

እንደ ኮሚሽነሩ አባባል፤ ይህ ሥራ ሲሠራ በሀገር ደረጃ ሰፋፊ የሆኑ ቅድሚያ የሚሰጣቸው ቦታዎች እና ዜጎች አሉ። በተለይ የመልሶ ማቋቋምና የመልሶ ግንባታ ሥራዎች ላይ



አምባሳደር ተሾመ ቶጋ

የንግዱ ማኅበረሰብ መሳተፍ አለበት። በተለይ በጦርነት ምክንያት የሰው ሀብት፣ ፋብሪካ እንዲሁም የንግድ እንቅስቃሴ በመጎዳቱ ወደ ነበረበት ለመመለስ የንግዱ ማኅበረሰብ ተሳትፎ ያስፈልጋል።

በመሆኑም የተረጋጋ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ ለማምጣት የንግዱ ማኅበረሰብ ሚና ወሳኝነት እንዳለው በመጥቀስ፤ ሠላምን ለማፅናት በሚደረገው ጥረት ውስጥ የንግዱ ማኅበረሰብ ከፍተኛ ሚና ሊጫወት እንደሚገባው አመልክተዋል።

የንግዱ ማኅበረሰብ የተደራጀ ከመሆኑ አንፃር ለሠላም ጥብቅና መቆም እንዳለበት በመጠቆም፤ በኢንተርፕራይዞችና በፋብሪካዎች አካባቢ ለቀድሞ ተዋጊዎች አስፈላጊውን የሥልጠና ዕድል በመስጠት አስተዋፅዖ እንዲያደርጉ፤ በተመሳሳይ በሚፈጠረው የሥራ ዕድል ላይ እንዲገቡ ማመቻቸት እንደሚገባም ጠቁመዋል።

የኢትዮጵያ ንግድ ማኅበራት ዘርፍ ምክር ቤት ፕሬዚዳንት ወይዘሮ መሰንበት ሸንቁጤ በበኩላቸው፤ የንግዱ ማኅበረሰብ ዛሬ ከተሐድሶ ኮሚሽኑ ጋር እንዳደረገው ተመሳሳይ ሥራ ከሌሎች ተቋማት ጋርም እንደሚቀጥል ተናግረዋል። ምክር ቤቱ ከሀገራዊ ተሐድሶ ኮሚሽን ጋር የሥራ ሰነድ መፈራረሙንም ገልፀዋል።

በመድረኩ ላይ ስምምነቱ መሬት ላይ ወርዶ እንዲተገበር ከበጀትና ከተሳትፎ አንፃር እያንዳንዱ የራሱን አስተዋፅዖ ካላደረገ በመንግሥት ብቻ ሊሠራ እንደማይችል ተጠቅሷል። ለዚህ ደግሞ የንግዱ ማኅበረሰብ ተሳትፎ የግድ መሆኑ ተመላክቷል።

# በኦሮሚያ ለ50 ሺህ የመንግሥት ሠራተኞች የሙያ ብቃት ፈተና ሊሰጥ ነው

ዋቅሹም ፍቃዱ

አዲስ አበባ፡- የኦሮሚያ ፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ኃይል ልማት ቢሮ በዘንድሮው ዓመት ለ50 ሺህ የመንግሥት ሠራተኞች የሙያ ብቃት ማረጋገጫ ፈተና ለመስጠት ማቀዱንና እስካሁን ለ12 ሺህ 50 ሠራተኞች መስጠቱን ገለጸ።

የቢሮው ምክትል ኃላፊ አቶ ያዕቆብ ታደሰ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፣ በተያዘው ዓመት ለ50 ሺህ የክልሉ የመንግሥት ሠራተኞች የሙያ ብቃት ማረጋገጫ ፈተና ለመስጠት አቅዶ እስካሁን ለ12 ሺህ 50 ሠራተኞች ፈተናውን ሰጥቷል።

ኦሮሚያ የአገልግሎት አሰጣጡን ቀልጣፋ ለማድረግ ብሎም ሠራተኞቹን ለማብቃት የሙያ ብቃት ማረጋገጫ ፈተና ቀደም ብሎ በ2012 ዓ.ም እንቅስቃሴ የጀመረ ሲሆን በ2015 ዓ.ም ወደ ተግባር በመግባት 16 ሺህ 500 ሠራተኞች ፈተናውን እንዲወስዱ አድርጓል ብለዋል።

እንደ አቶ ያዕቆብ ማብራሪያ፣ የፈተናው ዋና ዓላማ ሠራተኞቹን በማብቃት የደንበኞች እርካታን ማረጋገጥ ነው፡፡ አንድ ሠራተኛ ሥራውን በምን ሁኔታ እያከናወነ እንደሚገኝና በጠቅላላ እውቀት ራሱን ለማዳበር እያደረገ ያለው ጥረት ለማወቅ ፈተናው ጥሩ መለኪያ ሆኖ ተገኝቷል።

ፈተናው የአንድን ሠራተኛ ብቃት ለመለካት



አቶ ያዕቆብ ታደሰ

ብቻውን በቂ ስለማይሆን ሌሎች ተጨማሪ የመመዘኛ መስፈርቶችም ጥቅም ላይ ይውላሉ ሲሉም አስረድተዋል።

እስካሁን ባለው ሁኔታ በኦሮሚያ አንድን የመንግሥት ሠራተኛ ለመመዘን ፈተናው 25 በመቶ ክብደት የሚይዝ ሲሆን ትልቁ ክብደት ማለትም 75 በመቶ የሚይዘው ግን የሥራ ልምድ፣ የትምህርት ደረጃ፣ የሥራ አፈጻጸምና ሥነ ምግባር መሆኑን የተናገሩት አቶ ያዕቆብ፤ በተለይ የሥራ ልምድ ብቻውን 22 በመቶ ክብደት እንዳለው ተናግረዋል።

በፈተናው ማለፊያ ውጤት ያላመጣ ሠራተኛ ራሱን እንዲያበቃ ከደረጃው ዝቅ ብሎ ይመደባል ያሉት ምክትል ኃላፊው፤ ሆኖም ከሥራ ገበታ ይባረራል ተብሎ የሚናፈስ ወሬ መሠረተ ቢስ መሆኑን አስገንዝበዋል። በክልሉ ቀደም ብሎ ስለ ፈተናው ዓላማ በቂ ግንዛቤ ስለተሰጠ እስካሁን ያጋጠማቸው ችግር አለመኖሩ ብቻ ሳይሆን ሠራተኞችም በፈተናው ደስተኛ መሆናቸው ባደረጉት የዳሰሳ ጥናት ማረጋገጣቸውን ገልጸዋል።

ለኦሮሚያ ለሠራተኞች የሙያ ብቃት ማረጋገጫ መስጠት አዲስ ክስተት እንዳልሆነ ያወሱት አቶ ያዕቆብ፤ በኦሮሚያ በ2011 ዓ.ም በወጣው የመንግሥት ሠራተኞች አስተዳደር ሕግ ፈተናው እንዲሰጥ በጨፌ ኦሮሚያ መጽደቁን ጠቁመዋል። ፈተናው ስኬታማ እንዲሆንም የኦሮሚያ መንግሥት ዩኒቨርስቲ የአንበሳውን ድርሻ እየተጫወተ ነው ብለዋል።

ከፈተናው በተጓዳኝ ቢሮው ሐሰተኛ የትምህርት ማስረጃዎችን የማጣራት ሥራ እያከናወነ ይገኛል ያሉት ምክትል ቢሮ ኃላፊው፤ ከፌዴራል ትምህርትና ሥልጠና ባለሥልጣን ጋር በመሆን ከግል ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት በዲግሪና ከዚያ በላይ የተመረቁ የመንግሥት ሠራተኞች የትምህርት ማስረጃ የማጣራት ሥራ እየተሠራ ነው። በመቀጠልም ከመንግሥት ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት የተመረቁ የሠራተኞች ማስረጃ የማጣራት ሥራ ይጀመራል ብለዋል።

እስካሁን ባለው ሥራ የስምንት ሺህ ሠራተኞች ማስረጃ ከ24 መሥሪያ ቤቶች፣ ከአምስት ዞኖችና ከሁለት ከተማ መስተዳድሮች መሰብሰቡንም ገልጸዋል።

# ሁለት ሺህ የሚጠጉ አርሶ አደሮች የቡና ላኪነት ፍቃድ አግኝተዋል

አማን ረሺድ



አዲስ አበባ፡- ባለፉት አራት ዓመታት ሁለት ሺህ የሚጠጉ አርሶ አደሮች የቡና ምርት የላኪነት ፍቃድ ማግኘታቸው የኢትዮጵያ ቡናና ሻይ ባለሥልጣን አስታወቀ። ከ100 በላይ አርሶ አደሮች ምርታቸውን በቀጥታ ለውጪ ገበያ እየላኩ ይገኛል።

የባለሥልጣኑ የድህረ ምርት ዝግጅት መሪ ሥራ አስፈጻሚ አቶ መሐመድኑር አባጨብሳ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ ባለፉት አራት ዓመታት አንድ ሺህ 996 አርሶ አደሮች ምርታቸውን በቀጥታ ለውጪ ገበያ ማቅረብ እንዲችሉ የቡና ምርት የላኪነት ፍቃድ ማረጋገጫ ተሰጥቷቸዋል።

የቡና ግብይት ሰንሰለቱን ከማሳጠር አንጻር ሁለት ሄክታርና ከዛ በላይ የቡና ማሳ ያላቸው አርሶ አደሮች በቀጥታ ከላኪዎች ጋር ተገናኝተው እንዲሠሩ እየተደረገ ሲሆን፤ የበለጠ ውጤታማ እንዲሆኑ ሰፊ ድጋፍ እየተደረገ ይገኛል ብለዋል።

የቡና ላኪነት ፍቃድ ከወሰዱት አርሶ አደሮች መካከል ከ100 በላይ የሚሆኑ ቡናቸውን በቀጥታ ለውጭ ገበያ እየላኩ መሆናቸውን ገልጸዋል።

አርሶ አደሮቹ የተመቻቸውን ዕድል ተጠቅመው ሕይወታቸውን ከመቀየር ባለፈ ለሌሎች የሥራ ዕድል መፍጠር እንደቻሉ አመላክተዋል።

ባለሥልጣኑ ባለፉት አራት ዓመታት የሪፎርም ሥራዎችን መሥራቱን ጠቅሰው፤ የግብይት ሥርዓቱን በማዘመን፣ የቡና ምርት ጥራትን በማስጠበቅና ምርቱ ላይ እሴት መጨመር በመቻሉ ጥሩ መሻሻሎች መኖራቸውን ገልጸዋል።

ቡናን ጨምሮ ምርታቸውን ለውጪ ገበያ ለሚልኩ ላኪዎች የምርት ዝግጅት፣ የጥራት፣ የእሴት ጭመራና የብቃት ማረጋገጫ አገልግሎት እየሰጠ እንደሚገኝ አስረድተዋል።

የዓለም የቡና ገበያ ተለዋዋጭነትን መሠረት በማድረግ ተጨማሪ አዳዲስ የገበያ መዳረሻዎችን ወደ ቻይና፣ ኢንዶኔዢያና የተለያዩ የአውሮፓ ሀገራት የማስፋት ሥራ እየተሠራ መሆኑን አመላክተዋል።

የቡና ገበያ መቀዛቀዝን ተከትሎ የተወሰኑ አርሶ አደሮች ከላኪነት የመውጣት ስጋት እያጋጠማቸው መሆኑን ጠቁመው፤ ባለሥልጣኑ በተለያየ መንገድ ድጋፍ እያደረገላቸው በመሆኑ በገበያው ውስጥ እንዲቆዩ እየተደረገ መሆኑን ገልጸዋል።

ዜና

# የተቋማት ቅንጅታዊ አሠራር የከተማዋን ሠላምና ደህንነት ለማረጋገጥ አስችሏል

**ማሕሌት ብዙነህ**



አዲስ አበባ፡- የተቋማት ቅንጅታዊ አሠራር በመዲናዋ ዘላቂ ሠላምና ደህንነትን ማረጋገጥ ማስቻሉን የአዲስ አበባ ከተማ ሠላምና ፀጥታ ቢሮ አስታወቀ።

የአዲስ አበባ ሠላምና ፀጥታ አስተዳደር ቢሮ 2016 ዓ.ም በጀት ዓመት በስድስት ወራት በቅንጅት የተሠሩ ሥራዎች አፈፃፀም አስመልክቶ ከባለድርሻ አካላት ጋር በትናንትናው እለት ውይይት ተካሂዷል።

የአዲስ አበባ ከተማ ሠላምና ፀጥታ ቢሮ ኃላፊ ወይዘሮ ሊዲያ ግርማ በመድረኩ ላይ እንደገለጹት፤ ቢሮው የተሰጠው የከተማውን ሠላምና ፀጥታ የማስጠበቅ ኃላፊነት በአግባቡ እየተወጣ ነው። በተለይ ቢሮው በከተማው ከሚገኙ 20 ባለድርሻ ተቋማት ጋር በቅንጅት በመሥራት ላይ መሆኑ በከተማዋ ሠላምና ደህንነት ማረጋገጥ አስችሏል ።

ከባለድርሻ አካላት ጋር ቅንጅታዊ አሠራርን በማጠናከር ከተማዋ ደህንነቷ የተረጋገጠና ዘላቂ ሠላም ለማስፈን እየተሠራ ነው ያሉት ወይዘሮ ሊዲያ፣ በአሠራሩም የሚታዩ ጉድለቶችን በመለየትና በመፍታት የሕግ የበላይነትን ለማረጋገጥ እና ዘላቂ ሰላምና ደህንነትን ማስጠበቅ ያስችላል ብለዋል።

የቅንጅታዊ አሠራር መርሕ ተቋማት በግልጸኝነትና በኃላፊነት ስሜት የኅብረተሰቡን ፍላጎት ማርካትን መሠረት ያደረገ መሆኑን ገልጸው፤ ቅንጅታዊ አሠራር የአሠራር ድግግሞሽን ማስቀረትና የሀብት ብክነት ለመቀነስ ከማስቻሉም በላይ ተገቢውን አገልግሎት ለመስጠት ይረዳል ብለዋል።

ኅብረተሰቡን በሠላምና በልማት ተሳታፊ እንዲሆን በማድረግ ለፀጥታ ሥራ መሳካት ጉልህ አስተዋፅዖ የማድረጉ ተግባር ተጠናክሮ መቀጠል እንደሚገባው ወይዘሮ ሊዲያ አስታውቀዋል ።

የቢሮው የፀጥታና ኦፕሬሽን ዘርፍ ምክትል ቢሮ ኃላፊ አቶ ጌታሁን አበራ በመድረኩ ላይ ባቀረቡት ሪፖርት፤ በስድስት ወራት በተሠራ የቅንጅት ሥራ ዘርፈ ብዙ ሥራዎች መከናወናቸውን አስታውቀዋል።

ባለፉት ስድስት ወራት በሐሰተኛ ሰነድ፣ በሕገ ወጥ የጦር መሣሪያና የሰዎች ዝውውር ላይ የተሳተፉ 5 ሺህ 127 ተጠርጣሪዎችን መያዛቸውን ገልጸው፤ 3 ሺህ 100 ሕገወጥ ነጋዴዎች እና አንድ ሺህ 926 አዋኪ ድርጊት የፈጸሙ ድርጅቶች ላይ ርምጃ መወሰዱን ተናግረዋል።

ከ 98 በላይ ለአደጋ ስጋት የሆኑ ተፈጥሯዊና ሰው ሠራሽ ቦታዎችን የመለየት ሥራ መሠራቱንም አመልክተዋል።

ከ47 ሺህ በላይ ወጣቶችን በከተማው የፀጥታ ደህንነት ጉዳዮች ላይ ተሳታፊ ለማድረግና ግንዛቤ ለመፍጠር መቻሉንም አስታውቀዋል።

በከተማዋ ለወንጀል ምንጭና መስፋፊያ የሆኑ እንቅስቃሴዎችን የመቆጣጠርና የመከላከል ሥራ መሠራቱን አውስተው፤ የመልካም አስተዳደር ችግሮች በመፍታት ከተማዋ ሠላሟ የተጠበቀ እንዲሆን ከባለድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት መሠራቱንም ተናግረዋል። ይህንንም ቅንጅታዊ አሠራር ማጠናከር ይገባል ብለዋል።

# ‹‹የፍርድ ቤቶች አገልግሎት አሰጣጥ ሰብዓዊነትን ያስቀደመና ሥነ ምግባርን የተላበሰ መሆን ይገባዋል››

**- አበባ እምቢዓል**
**የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ምክትል ፕሬዚዳንት**

**ልጅዓለም ፍቅሬ**



አዲስ አበባ፡- የፍርድ ቤቶች አገልግሎት አሰጣጥ ሰብዓዊነትን ያስቀደመና የዳኝነት ሙያ የሚጠይቀውን ሥነ ምግባር የተላበሰ መሆን ይገባዋል ሲሉ የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ምክትል ፕሬዚዳንት አበባ እምቢዓል ገለጹ።

የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት 13ኛውን የቦሌ ምድብ ችሎት ትናንት አስመርቆ በይፋ ሥራ አስጀምሯል።

የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ምክትል ፕሬዚዳንት አበባ እምቢዓል በምርቃቱ ወቅት እንደገለጹት፤ የፍርድ ቤቶች አገልግሎት አሰጣጥ ሰብዓዊነትን ያስቀደመና ሙያው የሚፈልገውን ሥነ ምግባር የተላበሰ መሆን ይገባዋል።

እንደ ምክትል ፕሬዚዳንቷ ገለጻ፤ በቴክኖሎጂ የታገዘ የዳኝነት አገልግሎትና የፍርድ ቤቶች ተደራሽነት ምቹ የሥራ አካባቢን ለመፍጠርና ፍትሕን ከማስፈን ረገድ ትልቅ አስተዋፅዖ ቢኖረውም የሚፈለገውን ውጤት ለማምጣት አጋዥ እንጂ በራሳቸው ግብ አይደሉም። ከዚህ አንጻር አገልግሎት አሰጣጡ ሰብዓዊነትን ያስቀደመ፤ ትሕትናን የተላበሰና የዳኝነት ሥነ ምግባርን በተላበሰ መልኩ መሠራት እንዳለበት አሳስበዋል።

የፌደራል ፍርድ ቤቶች የዳኝነት አገልግሎት አሰጣጥን ውጤታማ ለማድረግ የዳኝነት የአገልግሎት ጥራት ላይ ትኩረት ተደርጎ እየተሠራ ነው ያሉት ምክትል ፕሬዚዳንቷ፤ የአምስት ዓመት መሪ እቅድ በመያዝ በሦስቱም ፍርድ ቤቶች የአገልግሎት ተደራሽነትን ለማሳደግ እየተሠራ ይገኛል ብለዋል።

እንደ ምክትል ፕሬዚዳንቷ ገለጻ፤ የዳኝነቱን ሥርዓት ዲጂታላይዝ የማድረግ ሥራ ከባለድርሻ አካላት ጋር እየተሠራ ነው ።

የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንት አቶ ፉዓድ ኪያር በበኩላቸው፤ የአሠራር ቅልጥፍናንና ተደራሽነት ለማሳደግ 13ኛ ምድብ ማደራጀት አስፈላጊ መሆኑን ተናግረዋል።

አቶ ፉዓድ አክለውም፤ የፌደራል የመጀመሪያ ፍርድ ቤት ድሬዳዋን ጨምሮ በ13 ምድብ ችሎቶች ቀልጣፋና ተዓማኒ የሆነ አገልግሎት እየሰጠ ይገኛል ብለዋል።

የቦሌ ምድብ ችሎት ከኅዳር 1 ቀን 2016 ዓ.ም ጀምሮ አገልግሎት ሲሰጥ መቆየቱን ያነሱት ፕሬዚዳንቱ፤ ምድብ ችሎቱ በአዲስ መልክ መደራጀቱ የጉዳዮች ፍሰት አስተዳደር መመሪያን በአግባቡ ለመተግበርና ፈጣን ውሳኔ ለማግኘት እንደሚያግዝ ጠቁመዋል።

እንደ አቶ ፉዓድ ገለጻ በአዲስ የተደራጀው ቦሌ ምድብ ችሎት ቀልጣፋና ዘመናዊ የአሠራር ሥርዓት አካቷል። የመልካም አስተዳደር ችግሮች ለመቅረፍ የሚያግዙ የአሠራር ሥርዓቶች እንዲሁም የአንድ መስኮት አገልግሎት ማካተቱን ፕሬዚዳንቱ ጨምረው ገልጸዋል።

በተጨማሪም በምድብ ችሎቱ ዘመናዊ ቴክኖሎጂ በመጠቀም ፋይል የመክፈት ሂደት፣ የእያንዳንዱ ጉዳይ የጊዜ ገደብ የሚቆጣጠር ቴክኖሎጂ በማካተት እንዲሆም የአስማሚነት የሥራ ክፍል ተካቶ ባለፈው አንድ ወር ከ12 በላይ ጉዳዮችን መፍታት እንደተቻለ አቶ ፉዓድ ገልጸዋል።

# 84ኛውን የአገው ፈረሰኞች ፌስቲቫል ለማክበር ዝግጅት ተጠናቋል

## -በፌስቲቫሉ ከሁለት ሺህ በላይ ፈረሰኞች ይሳተፋሉ

**ልጅዓለም ፍቅሬ**

አዲስ አበባ፡- ዘንድሮ ለ84ኛ ጊዜ የሚካሄደውን የአገው ፈረሰኞች ፌስቲቫል ለማክበር ቅድመ ዝግጅት መጠናቀቁን የአዊ ብሔረሰብ ዞን አስተዳደር ባሕልና ቱሪዝም ጽሕፈት ቤት አስታወቀ። በፌስቲቫሉ ከሁለት ሺህ በላይ ፈረሰኞች እንደሚሳተፉ ቢሮው ጨምሮ ገልጿል።

የአዊ ብሔረሰብ ዞን አስተዳደር ባሕልና ቱሪዝም ቢሮ ኃላፊ አቶ ለይኩን ሲሳይ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንዳስታወቁት፤ ዘንድሮ ለ84ኛ ጊዜ ለሚከበረው የአገው ፈረሰኞች ፌስቲቫል ዝግጅት ተጠናቋል።

በዓሉ ‹‹የሰላም አርበኝነት ለወንድማማችነት›› በሚል መሪ ሃሳብ ጥር 22 እና 23 ይከበራል ብለዋል።

በዓሉን ለቱሪስት አመቺ በሆነ መንገድ ለማክበር ዝግጅት ሲደረግ መቆየቱን የጠቀሱት አቶ ለይኩን፤ ለበዓሉ አስፈላጊውን ሁሉ ለሟሟላት በዞኑ ዋና አስተዳዳሪ የሚመራ ዐቢይ ኮሚቴ ተቋቁሞ ወደ ሥራ የገባ መሆኑን ጠቁመዋል።

አቶ ለይኩን አክለውም፤ በዓሉን ከማክበር ጎን ለጎን የዞኑን ቱሪዝም ለማነቃቃትና ለማስተዋወቅ የተለያዩ ባሕላዊ ምግቦችና የዕደ ጥበባት ሥራዎች በኤግዚቢሽን መልክ እንደሚቀርቡ ገልጸዋል።

በበዓሉ ወቅት የመሠረተ ልማትና የፀጥታ ችግሮች እንዳያጋጥሙ ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር እየተሠራ እንደሆነም ነው አቶ ለይኩን ያመላከቱት።

እንደ አቶ ለይኩን ገለጻ፤ ጥር 22 በዓሉን አስመልክቶ ‹‹የአገው ፈረሰኞች በዓል ለሰላም ግንባታ›› በሚል መሪ ሃሳብ የፓናል ውይይት ይካሄዳል።

በመጨረሻም በወረዳ ደረጃ ጥር 26 በዓንዓ ወረዳ እንደሚከበር አቶ ለይኩን ተናግረዋል።

በዓሉ የተለያዩ ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ችግሮች የሚፈታበት ነው ያሉት አቶ ለይኩን፤ ዘንድሮም ባሕላዊ እሴቱን በጠበቀ መልኩ ለማክበር በየደረጃው ዝግጅት ተጠናቋል ብለዋል።

እንደ አቶ ለይኩን ገለጻ፤ በዓሉ የዞኑን ቱሪዝም ከማነቃቃትና ማኅበራዊ መስተጋብር ከማጎልበት በተጨማሪ ኢኮኖሚያዊ መነቃቃት ይፈጥራል።

አቶ ለይኩን አክለውም፤ ከመንደር ጀምሮ እስከ ዞን ድረስ ስድስት ሺህ 200 የባሕላዊ አመራሮች አሉት ያሉ ሲሆን፤ እነዚህ አመራሮች በአካባቢው ሰላም መፍጠር ላይ ትኩረት አድርገው የሚሠሩ ናቸው ሲሉም ተናግረዋል።

አቶ ለይኩን፤ የአገው ፈረሰኞች ማኅበር ከ62 ሺህ 200 መቶ አባላት በላይ ያሉት መሆኑን ጠቅሰው፤ በዘንድሮው ፌስቲቫል ከሁለት ሺህ በላይ ፈረሰኞች እንደሚሳተፉ አስታውቀዋል።

በዓሉ የሕዝብ በዓል በመሆኑ ሕዝቡ የበዓሉን ባሕላዊ እሴት ጠብቆ እንዲያከብር እንዲሁም ለሚመጡ እንግዶች በኢትዮጵያዊ ጨዋነት ተቀብሎ እንዲያስተናግዱ ጥሪ አድርገዋል።

# ታጣቂዎች ጠብመንጃቸውን በማስቀመጥ ሕዝቡን ከቀውስ ለማውጣት እንዲጥሩ ኢዜማ ጥሪ አቀረበ

## - ለረሀብ የተጋለጡ ዜጎችን ለመታደግ አፋጣኝ መፍትሔ ሊወሰድ ይገባል

**ሄለን ወንድምነው**

አዲስ አበባ፡- በሀገሪቱ የተለያዩ ክፍሎች የሚገኙ ታጣቂዎች ጠብመንጃቸውን በማስቀመጥ ሕዝቡን ከገባበት ቀውስ ለማውጣት የድርሻቸውን ሊወጡ እንደሚገባ የኢትዮጵያ ዜጎች ለማኅበራዊ ፍትሕ ፓርቲ (ኢዜማ) ጥሪ አቀረበ። በትግራይ ክልል እና ሌሎች አካባቢዎች ለረሀብ የተጋለጡ ዜጎችን ለመታደግ አፋጣኝ እርምጃ መወሰድ አለበትም ብሏል።

የኢትዮጵያ ዜጎች ለማኅበራዊ ፍትሕ (ኢዜማ) ፓርቲ በወቅታዊ ሀገራዊ ጉዳዮች ላይ ለመገናኛ ብዙኃን ትናንት መግለጫ ሰጥቷል። የኢዜማ ፓርቲ ዋና ጸሐፊ አቶ አበበ አካሉ በሰጡት መግለጫ እንዳስታወቁት፤ በሀገሪቱ አንዳንድ አካባቢዎች በሚፈጠሩ ግጭቶች ምክንያት የግብርና፣ የንግድ፣ የኢንቨስትመንት፣ የትምህርት እና ሌሎች ሥራዎች ተስተጓጉለዋል።

በነፃ አውጪ ስም በየአካባቢው ታጣቂ ቡድኖች እየበዙ መምጣታቸውን ገልጸው፤ ይህም የእርስ በርስ እልቂትን ለማስፋፋትና ሀገሪቱን ለመበታተን ለሚፈልጉ የውጭ ኃይሎች ምቹ ሁኔታ መፍጠሩን አስታውቀዋል።

በተጨማሪም ግጭቱ የግብርና፣ የንግድ፣ የኢንቨስትመንት፣ የትምህርት እና ሌሎች ሥራዎችን የተስተጓጎለ ሲሆን፤ ግጭቶች በዚሁ ከቀጠሉ ሀገሪቱ ልትወጣው የማትችለው የሕልውና አደጋ ውስጥ ልትገባ እንደምትችል አስረድተዋል።

ለዚህ ችግር መነሻ የሆኑ ታጣቂዎች ጠብመንጃቸውን በማስቀመጥ ቢያንስ "ቆመንለታል" የሚሉትን ሕዝብ ከገባበት አጠቃላይ ቀውስ ለማውጣት የበኩላቸውን ድርሻ ሊወጡ እንደሚገባ ገልጸዋል።

ጦርነት ፋይዳ እንደሌለው በመረዳት ለዓመታት የዘለቀውን ግጭት በማስቆም ለሰላም መስፈን መጣር ይገባልም ብለዋል።

ጠብመንጃ አንግተው ውጊያ ውስጥ የሚገኙ ታጣቂዎች ለሠላም የትኛውንም ዋጋ ለመክፈል ቁርጠኛ በመሆን ሕዝቡ ከገባበት ስቃይና እንግልት ማውጣትን ቅድሚያ የሚሰጡት ተግባራቸው ሊያደርጉት እንደሚገባ አስገንዝበዋል።

የሀገሪቱን ዘላቂ ሰላምና ደህንነት ለማስከበር የሁሉም ኢትዮጵያውያን አስተዋፅዖ ከፍተኛ ነው ያሉት አቶ አበበ፤ የጋራ ቤታችንን ኢትዮጵያን በአንድነት ለማቆም መደበኛ የፀጥታ መዋቅሮችን ለማጠናከር የሚደረጉ ድጋፎችን አጠናክሮ ማስቀጠል እንደሚገባ አመላክተዋል።

ግጭት መቀስቀስ እና "በለው በለው" ማለት ሁላችንንም ከማንወጣው የግጭት ማጥ ውስጥ እንደሚከትተን መገንዘብ ይገባል ያሉት ዋና ጸሐፊው፤ ለሰላም መስፈን መገናኛ ብዙኃን፣ አክቲቪስቶች፣ ፖለቲከኞችና ሌሎች ባለድርሻ አካላት ኃላፊነታቸውን መወጣት አለባቸው ብለዋል።

መንግሥትም በቤኒሻንጉል ጉሙዝ፣ በደቡብና በኦሮሚያ ክልል አንዳንድ አካባቢዎች ውጤት ያመጡ የሠላም ማስፈን ተሞክሮዎችን በመቀመር ያደረገውን ጥረት በሌሎች አካባቢዎችም ተግባራዊ ሊያደርግ እንደሚገባ አመላክተዋል። ሕዝቡን በማስተባበር ለዘላቂ የሠላምና ደህንነት መጠበቅ የሚያግዙ ሥራዎችን በስፋት ሊያከናውን እንደሚገባም ጨምረው ገልጸዋል።

የፖለቲካ ግባችንም ሆነ የትግል ስልታችን ወደ ሠላም እንጂ ወደሁከት እንደማይወስደን ማረጋገጥ የሞራል ከፍታ ማሳያ ስለሆነ ምግባራችን ሁሉ ሠላም አዋላጅ ሊሆን ይገባል ሲሉ ተናግረዋል።

መንግሥትና ሕዝብ ሆድና ጀርባ ሳይሆን እጅና ጓንት እንዲሆኑ የፀጥታ አካላት ሕግ ማክበርና ሰብዓዊነትን መላበስ ይኖርባቸዋል ያሉት ዋና ጸሐፊው፤ በተለይም የፌደራል ፖሊስ መሪ ቃል የሆነው በጀግንነት መጠበቅ፤ በሰብዓዊነት ማገልገል የሚለው ሀሳብ በተግባር ሊመረኮዝ እንደሚገባ አስገንዝበዋል።

በደቡብ ኢትዮጵያ አካባቢዎች የሚገኙ የኢዜማ አባላትና ደጋፊዎች ላይ እየደረሰ ያለው በደል አሳሳቢ ደረጃ መድረሱን ገልጸው፤ ይህ አካሄድ መድብለ ፓርቲ ሥርዓትን ለመገንባት እና በሀገሪቱ መቃቃርንና መካረርን የሚያላብስ ነው ብለዋል።

የመንግሥት ኃላፊዎች ድርጊቱን በአስቸኳይ እንዲቆም በማድረግ ሀገራዊ መግባባትን እና የመድብለ ፓርቲ ሥርዓትን በመገንባት ረገድ የድርሻቸውን እንዲወጡ ጠይቀዋል።

በሌላ በኩል በትግራይ ክልል እና በሌሎች አካባቢዎች ለረሀብ የተጋለጡ ዜጎችን በአስቸኳይ ለመታደግ ኢትዮጵያውያንና ዓለም አቀፉ ማኅበረሰብ አፋጣኝ እርምጃ ሊወሰድ ይገባል ብለዋል።

ጉዳዩን የቁጥር ጨዋታና የፖለቲካ ትርፍ ማግኛ ከማድረግ ለረሀብ የተጋለጡ ዜጎችን ለመታደግ አስቸኳይ ሀገር አቀፍ ርብርብ ከማድረግ ባለፈም ዜጎች የመፍትሔው አካል እንዲሆኑ መንግሥት ተገቢውን መረጃ በተገቢው ሰዓት ማድረስ ይጠበቅበታል ሲሉ አሳስበዋል።

# ስሀገራዊ ምክክሩ...

ከ1ኛ ገጽ የዞረ

ፖሊሲዎችን አንጥሮ በማውጣት ለመመካከርና ሀገራዊ መግባባት ላይ ለመድረስ ምሑራን ዋነኛ ተሳታፊ መሆን እንደሚጠበቅባቸው ተናግረዋል።

ሀገራዊ ምክክሩ ስኬታማ ከሆነ ሀገራችንን ወደተሻለ ምዕራፍ የምናሻግርበት ታላቅ ታሪካዊ ድል ነው ያሉት ምክትል ዋና ኮሚሽነሯ፤ ይህ ካልተሳካም በትውልድና በታሪክ ተወቃሽ የሚያደርግ በመሆኑ ምሑራን የተገኘው ዕድል እንዳይመክን ድርብ ኃላፊነታችሁን በመወጣት ለምክክሩ ስኬታማነት ርብርብ ማድረግ ይጠበቅባችኋል ብለዋል።

ኮሚሽኑ አካታችና አሳታፊ ውይይት ለማድረግ ቁርጠኛ መሆኑን የጠቆሙት ምክትል ዋና ኮሚሽነሯ፤ ሀገራዊ ምክክሩ በባለድርሻ አካላትና በማኅበረሰቡ ዘንድ ቅቡልነት እንዲኖረው ለማስቻል አሳታፊ የልየታ ሥራ እየተሠራ መሆኑንም ተናግረዋል። አጀንዳዎችን በማወያያ መድረኮች ለማሰባሰብ ኮሚሽኑ ዝግጅቱን ማጠናቀቁንም አክለው ገልጸዋል።

በመድረኩ ንግግር ያደረጉት የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ተጠባባቂ ፕሬዚዳንት ሳሙኤል ክፍሌ(ዶ/ር) በበኩላቸው የማያግባቡ ጉዳዮችን በውይይት በመፍታት ሀገራዊ ብልጽግናን ለማረጋገጥ የምሑራን ሚና ከፍተኛ መሆኑን ገልጸዋል።

ሀገራችን በረዥሙ ታሪኳ ውስጥ በርካታ ሀገረ መንግሥቱን የሚፈታተኑ ጉዳዮች ገጥመዋት በሕዝቦቿ አስተዋይነት አልፋለች ያሉት ሳሙኤል(ዶ/ር)፤ አሁንም በርካታ ውይይትና ንግግር የሚፈልጉ ጉዳዮች በመኖራቸው መላው ሕዝባችን ተወያይቶ መግባባት ላይ መድረስ እንዳለበት አስረድተዋል።

በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የሚኖሩ የጥናት መድረኮች ለምክክሩ አስተዋፅዖ እንዲኖራቸው ለማድረግ በርካታ የውይይት መድረኮችን በመዘጋጀት ላይ መሆናቸውን የተናገሩት ተጠባባቂ ፕሬዚዳንቱ፤ በተለይም ለሀገረ መንግሥቱ ግንባታ፣ ለዘላቂ ሠላም፣ ለብልጽግና እና ለልማት ልዩ ትኩረት የሚሰጡ አጀንዳዎች ትኩረት እንደተሰጣቸው ገልጸዋል።

በመድረኩ "የሀገራዊ ምክክር ዕይታዎች፣ ምዘናዎችና ዓለማቀፋዊ ልምዶች"፣ "የምክክር መንገድ አግባብነት ለኢትዮጵያ ችግሮች "፣ "ምክክር በኢትዮጵያ ልምድ ተስፋና ስጋቶች" እና "የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ምሑራን ሚና ለኢትዮጵያ ሀገራዊ ምክክር ስኬት" የሚሉ ጥናታዊ ጽሁፎች ቀርበው ውይይት ተደርጎባቸዋል።

# ከጥር እስከ መጋቢት...

ከ1ኛ ገጽ የዞረ

እንዲሁም በኦሮሚያ፣ በደቡብ ኢትዮጵያ እና ደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ የሚገኙ የድርቅ እና የግጭት አደጋ ተጎጂዎች መሆናቸውን ገልጸው፤ 2 ነጥብ 6 ሚሊዮን የሚሆኑት በሌሎች የሀገሪቱ አካባቢዎች በጎርፍ፣ ግጭት እና የድርቅ አደጋዎች ጉዳት የደረሰባቸው የኅብረተሰብ ክፍሎችን የሚያካትት መሆኑን አመልክተዋል።

አጠቃላይ የሚያስፈልገው የምግብ መጠን አንድ ሚሊዮን 118 ሺህ 700 ኩንታል መሆኑን ገልጸው፣ ይህም በብር ሲሰላ 9 ነጥብ 2 ቢሊዮን የሚገመት መሆኑን አስታውቀዋል።

ከሐምሌ ወር 2015 ዓ.ም እስከ ታኅሣሥ ወር 2016 ዓ.ም ባሉት ስድስት ወራት ከመንግሥትና አጋር አካላት በተገኘ 15 ቢሊዮን ብር የገንዘብ ድጋፍ ለሦስት ተከታታይ ዙሮች አስቸኳይ የሰብዓዊ ድጋፍ ለሚያስፈልጋቸው ዜጎች ድጋፍ መደረጉን ሚኒስትር ዴኤታዋ አመልክተው፤ በዚህም አንድ ነጥብ 7 ሚሊዮን ኩንታል ምግብ በዓይነትና የሁለት ቢሊዮን ብር የጥሬ ገንዘብ ድጋፍ መቅረቡን አውስተዋል።

ከተሰጠው የምግብ ድጋፍ ውስጥ 77 በመቶ በመንግሥት፣ 23 በመቶ በአጋር አካላት አማካኝነት የተሸፈነ ነው ያሉት ሚኒስትር ዴኤታዋ፤ ከተሠራጨው ሁለት ቢሊዮን ብር ውስጥ 40 በመቶ መንግሥት 60 በመቶ ከዓለም ባንክ በተገኘ ድጋፍ የተሸፈነ እንደሆነ ጠቁመዋል።

ባለፈው ሳምንት በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ እምነት ተከታዮች ዘንድ ትልልቅ ሃይማኖታዊ የአደባባይ በዓላት የሆኑት የከተራ፣ የጥምቀትና የቃና ዘገሊላ መከበራቸውን አስታውሰው፤ እነዚህ በዓላት በሁሉም የኢትዮጵያ ጫፍ በታላቅ ድምቀት ያለ ምንም የፀጥታ ችግር ሃይማኖታዊና ባሕላዊ ትውፊታቸውን ጠብቀው መከበራቸውን ተናግረዋል።

ለዚህም የሃይማኖት አባቶች፤ የፀጥታ ተቋማትና አባላት፣ ወጣት የእምነቱ ተከታዮች እና መላው ሕዝብ ምስጋና አቅርበዋል።

በቅርቡ በአዲስ አበባ ለሚካሄደው የአፍሪካ ኅብረት የመሪዎች ጉባኤም ሰፊ ቅድመ ዝግጅት እየተደረገ ነው ያሉት ሚኒስትር ዴኤታዋ፤ ጉባኤውን በስኬት ለማጠናቀቅ ኅብረተሰቡ ከፀጥታ አካላት ጋር ተባብሮ በመሥራት የኢትዮጵያን ብሎም የአዲስ አበባን የዲፕሎማሲ ማዕከልነት ዳግም ለዓለም እንዲያሳይ ጥሪ አቅርበዋል።

# "በቀጣናው በጋራ...

ከ1ኛ ገጽ የዞረ

መለስ ዓለም (ዶ/ር) ትናንት ለጋዜጠኞች በሰጡት መግለጫ እንደገለጹት፣ ኢትዮጵያ ስለ ባሕር በር ያላትን አቋም በተመለከተ ተቀማጭነታቸውን አዲስ አበባ ላደረጉ ዲፕሎማቶች የኢትዮጵያን ፍላጎት በሚገባ ማስረዳት ተችሏል። በዚህም በርካታ አወንታዊ ምላሾች ተገኝተዋል።

እንደ አምባሳደር መለስ ገለጻ፤ በቀጣናው በጋራ ለመልማት ፍላጎት ካለው ሀገር ጋር ኢትዮጵያ ለመወያየትና ለመደራደር ዝግጁ ናት። በተደጋጋሚ በመሪዎች ደረጃ የተገለጸው ኢትዮጵያ ሁልጊዜ ለውይይትና ለምክክር በሯ ክፍት መሆኑን ነው። በተለይ ደግሞ ቀጣናው የተረጋጋ እንዲሆን ለውይይት ቅድሚያ ሊሰጥ ይገባል።

ለአፍሪካዊ ችግር አፍሪካዊ መፍትሔ ያስፈልጋዋል ያሉት አምባሳደር መለስ፤ ሆኖም የመግለጫ ጋጋታ ለውጥ አይኖረውም፤ በኢትዮጵያ በኩል ቀውስን ማርገብ ጠቃሚ ነው የሚል አቋም አለ ብለዋል።

አምባሳደር መለስ እንዳሉት፤ ከኢትዮጵያውያን በላይ ለሶማሊያውያን የሚያስብ አይኖርም፤ ሶማሊያ የተረጋጋች ሀገር እንድትሆንና ጠንካራ ተቋማት እንዲኖራት ኢትዮጵያውያን ዋጋ እየከፈሉ ይገኛሉ።

የባሕር በር ስምምነትን በተመለከተ የመግለጫ ጋጋታ ኢትዮጵያ ላይ የሚፈጥረው ነገር የለም ያሉት አምባሳደሩ፤ ኢትዮጵያ ትልቅ ሀገር በመሆኗ በትንሽ ማዕበል አትናጥም ሲሉም ገልጸዋል።

"ባለፉት ሦስት ዓመታት ያለፍንበት ሁኔታ ሌሎች ሀገራት ያልፉበታል ብሎ መገመት ያዳግታል። እንዲሁም ባለፉት ሺህ ዘመናት ኢትዮጵያ የገጠማትን ችግር በርካታ ሀገራት አያልፉትም። የዓረብ ሊግና የግብፅ መግለጫ ብዙም የሚያመጣው ለውጥ የለም፤ ኢትዮጵያ በሰላማዊ መንገድ በጋራ መልማትን ትፈልጋለች" ሲሉም ገልጸዋል።

በተያያዘ ዜና በሳይንስ ሙዚየም የተከፈተው የዲፕሎማሲ ሳምንት በብዙዎች እየተጎበኘ ነው ያሉት ቃል አቀባዩ፤ ከአዲስ አበባ ውጭ ባሉ ዜጐች ጭምር እየተጎበኘ መሆኑን ገልጸዋል።

ኤግዚቢሽኑ ከተከፈተ ጀምሮ የ126 ተቋማት ሠራተኞችና የሥራ ኃላፊዎች፣ 700 ዲፕሎማቶችና የሁለተኛ ትውልድ ኢትዮጵያን እንደጐበኙት ጠቁመው፤ ከ151 በላይ ጋዜጠኞች እንደዘገቡትም ተናግረዋል። በተመሳሳይ የውጭ ሀገር ሚዲያዎችም ሽፋን እንደሰጡት ገልጸዋል።

የፕሪቶሪያን የሰላም ስምምነት በተመለከተ አምባሳደሩ እንደገለጹት፤ ትልቁ ነገር በስምምነቱ ሰላም መምጣቱ ነው። ይሁን እንጂ የድህረ ጦርነት የሰላም ግንባታ ብዙ ሥራ ይጠይቃል። ኢትዮጵያ ብቻ ሳትሆን ሌሎች ዓለም አቀፍ ተቋማት ጭምር አስተዋፅዖ ማድረግ አለባቸው ብለዋል።

"በሰላም ስምምነቱ ሰላም መጥቷል፤ የተፈናቀሉ የሰብዓዊ ድጋፍ እንዲያገኙ ሆኗል፣ ተቋርጠው የነበሩ አገልግሎቶች ሥራ መጀመራቸውና የመሠረተ ልማት ግንባታ መጀመሩ ትልቅ ውጤት ነው" ያሉት አምባሳደር ዶክተር መለስ፤ የፕሪቶሪያው የሰላም ስምምነት አፈጻጸም ሙሉ ለሙሉ የተሟላ ነው ማለት ስለማይቻል የሚጎድሉ ነገሮችን በጋራ መሙላት እንደሚያስፈልግም ጠቁመዋል።

# ርዕሰ አንቀፅ

## በውጭ ሀገራት የሚኖረው ሁለተኛ ትውልድ ለሀገሩ ልማት የሚጠበቅበትን ሚና ሊወጣ ይገባል!

ባለፉት አምስት ዓመታት ኢትዮጵያ በዲፕሎማሲው መስክ ካሳየቻቸው እምርታዎች አንዱ ዜጋ ተኮር ዲፕሎማሲ መከተሏ ነው፡፡ አዲስ በሆነው በዚህ ዜጋ ተኮር ዲፕሎማሲ በአስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ የነበሩ በርካታ ኢትዮጵያውያን ወደ ሀገራቸው በክብር ለመመለስ ከመቻሏም በላይ በአሁኑ ወቅት በውጭ ሀገራት የሚኖሩ ሁለተኛ ትውልድ ኢትዮጵያውያን ወደ ሀገራቸው መጥተው ታሪካቸውን፤ ወግና ባሕላቸውን እንዲያውቁ መንግሥት ጥሪ አቅርቧል፡፡ ይህንኑ ጥሪ ተቀብለው እየመጡት ላሉትም የአየር ትኬትና የሆቴል መስተንግዶ ቅናሽ ከማድረግ ጀምሮ የተለያዩ ማበረታቻዎች እየተደረጉ ነው፡፡

በውጭ ሀገራት የሚኖሩ ሁለተኛ ትውልድ ኢትዮጵያውያን በሦስት ዙሮች ወደ ሀገር ቤት እንዲገቡ ጥሪ ቀርቧል፡፡ በመንግሥት የተደረገውን ጥሪ ተከትሎም ከታኅሣሥ 20 ቀን 2016 ዓ.ም እስከ መስከረም ወር 2017 ዓ.ም መጨረሻ ቀናት በሦስት ዙሮች በርካታ ቁጥር ያላቸው የሁለተኛው ትውልድ አባላት ወደ ኢትዮጵያ ይመጣሉ ተብሎ ይታሰባል፡፡ የሁለተኛው ትውልድ ወደ ሀገር ውስጥ መምጣትም በርካታ ትሩፋቶችን ይዞ የሚመጣ ነው፡፡

የመጀመሪያውና ዋነኛው በውጭ ሀገራት የሚኖሩ ሁለተኛ ትውልድ ኢትዮጵያውያን ሀገራቸውን እንዲያውቁ ዕድል ይሰጣቸዋል፡፡ ኢትዮጵያ የሰው ልጅ መገኛ፤ በቅኝ ግዛት ያልተገዛች ብቸኛዋ ሀገር እና የጥቁር ሕዝቦች ኩራት፤ በተፈጥሮ ሃብት የታደለች፤ በዩኒስኮ 16 ቅርሶችን ያስመዘገበች ብቸኛዋ አፍሪካዊት ሀገር፤ የአፍሪካ ዋንጫ መሥራች፤ በኮርያ ፤ በኮንጎ እና በሌሎች የአፍሪካ ሀገራት ሰላም በማስከበር አንቱታን ያገኘች ሀገር ነች፡፡ ይህ ታሪክ ደግሞ ሀገር ውስጥ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን ብቻ ሳይሆን የሁለተኛው ትውልድ መኩሪያ ታሪክ ጭምር ነው፡፡

ሁለተኛው ትውልድ በማኅበራዊም ሆነ በሥነ ልቦና ረገድ ጠንካራ ማንነት ሊገነባ የሚችለው ታሪኩን፤ ባሕልና ወጉን መረዳት ሲችል ነው፡፡ ይህ ትውልድ ከኢትዮጵያ ይዞት የሄደ ባሕልና ማኅበራዊ ሕይወት ስለሌለው እና ሙሉ ለሙሉ በውጭ ባሕል ያደገ በመሆኑ እንደ ቀደመው ትውልድ ጠንካራ ስብዕና አይኖረውም፡፡ ስለዚህም ጥሪውን ተከትሎ ሲመጣ የሀገሩን ታሪክ፤ ወግና ባሕል እንዲሁም ማኅበራዊ ሕይወት በቀላሉ በመረዳት ከማንነት ቀውስ ይላቀቃል፤ በራሱና በሀገሩ ይኮራል፡፡ ይህ ዕድልም ሁለተኛ ትውልድ ኢትዮጵያውያን ከወላጆቻቸው ሀገር ጋር ቁርኝት እንዲፈጥሩ፣ መነሻ ሀገራቸውን በአግባቡ እንዲረዱና በማንነታቸው እንዲኮሩ ያስችላቸዋል፡፡

ማንኛውም ትውልድ መነሻ ያስፈልገዋል፡፡ በውጭ ሀገራት የሚኖሩ ሁለተኛ ትውልድ ኢትዮጵያውያን ወደ ሀገር ውስጥ መምጣት ከሀገራቸው ጋር ቋሚ ግንኙነት እንዲፈጥሩ እና መነሻቸውንም እንዲያውቁ ያደርጋል፡፡ ሁለተኛው ትውልድ ከኢትዮጵያ ይዞት የሄደ ባሕልና ማኅበራዊ ሕይወት ስለሌለው ለጊዜው ለመኩራት የሚሞክረው የሚችለው ባለበት ሀገር ታሪክና ባሕል ነው፡፡ ይህ ደግሞ የራስ ባልሆነ ታሪክ፤ ወግና ባሕል ለመድምቅ መሞከር ግንጥል ጌጥ ከመሆን አያልፍምና አሁን የተሰጠው ዕድል ወደ ኢትዮጵያ መጥቶ በአባት አያቶቹ ታሪክ እንዲኮራ ዕድል ይፈጥርለታል፡፡

በሦስት ዙር ወደ ኢትዮጵያ የሚመጣውም የሁለተኛው ትውልድ አባቶቻቸውና አያቶቻቸው ያቀኗትን ሀገር እንዲያውቁና የትውልድ ቅብብሎሽ እንዲኖር ያደርጋል፡፡ የወላጆቻቸው ሀገር ክብርና ዝና በአካል ተገኝተው እንዲረዱ ያስችላል፡፡ ኢትዮጵያ በትውልድ ቅብብሎሽ የጸናች ሀገር ናት፡፡ የትላንቱ ትውልድ በከፈለው መስዋዕትነት የጥቁር ሕዝቦች የነፃነት አክሊል ሆና ዘለቀች ሀገር ነች፡፡ ይህችን ድንቅ ሀገር በአካል ተገኝቶ ማየትና መረዳት ከዕድልም በላይ ነው፡፡

በውጭ ሀገራት የሚኖሩ ሁለተኛ ትውልድ ኢትዮጵያውያን ወደ ሀገራቸው መግባት ሀገራቸው ላይ ዕውቀታቸውንና ገንዘባቸውን እንዲያፈሱ ዕድል ይሰጣል፡፡ አዲሱ ትውልድ በሠለጠኑት ዓለማት ያገኘውን የሳይንስና ቴክኖሎጂ ዕውቀት ወደ ሀገሩ በማምጣት ኢትዮጵያ ውስጥ የሚታዩትን ችግሮች ደረጃ በደረጃ ለመፍታትም ዕድል ይሰጠዋል፡፡

ሁለተኛው ትውልድ ሀገሩን የማወቅ ዕድል ማግኘቱ ትልቅ ዕድል ከመሆኑም ባሻገር ለኢትዮጵያም ትልቅ ተስፋ ነው፡፡ አዲሱ ትውልድ ትምህርት ለማስፋፋት፤ መንገዶችን ለመሥራትና ተደራሽ ለማድረግ፤ ኢንቨስትመንትን ለማሳደግ በአጠቃላይ የተጀመረውን ልማት ወደ ተሻለ ደረጃ ለማድረስ የማይተካ ሚና ይጫወታል፡፡

ስለሆነም በውጭ ሀገራት የሚኖሩ ሁለተኛ ትውልድ ኢትዮጵያውያን ወደ ሀገራቸው እንዲገቡ የተደረገው ጥሪ ተጠናክሮ ሊቀጥል ይገባል፡፡ የተገኘውን ዕድል በመጠቀም በሀገሩ ልማት ላይ የማይተካ ሚና መጫወት ይጠበቅበታል!


# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስፈጻሚ**

ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22

ኢሜል ፡- epa@press.et

**ዋና አዘጋጅ**

አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**

ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ

ወረዳ 06

የቤት ቁጥር 319

ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et

ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**

ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com

ስልክ - 011-126-43-41

ፋክስ - 011-811-13-15

የዝግጅት ክፍል ፋክስ - 251-011-1-56-98-62

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**

ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ

ስልክ፡- 011 126 4200

Email:- wendweson.shimelis@press.et

wendwesonshimelis@gmail.com

**የዜና ማዕከል ዋና አዘጋጅ**

ወርቁ ማሩ

Email:- workumaru2@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**

- ኃይሉ ሣህለድንግል
- እስማኤል አረቦ
- ቦጋለ አበበ

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**

ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73

ፋክስ - 011-126-58-12

ቴሌግራም - 097- 608-47-07 - Press

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**

ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ** :- ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


# ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው፡፡በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም፡፡

## መንጋቱ ሳይቀር ...

**በሰላም**

በሚገርም፣ በሚያናድድና በሚያስቆጭ ሁኔታ ኢትዮጵያ ወደብ አልባ ሆና ከሦስት አሥርተ ዓመታት በላይ ቆይታለች። ይሄ የኢትዮጵያ ወደብ ጉዳይ በሀገር ቤትም ሆነ በውጭው ዓለም ማኅበረሰብ እሳቤ ግብዓተ መሬቱ የተፈፀመና ያለቀለት ይመስል ነበር። በዚህ ጭጋግ በበዛበትና ደመናው በከበደበት ሰዓት ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) ጉዳዩን የአደባባይ አጀንዳ አደረጉት።

ጠቅላይ ሚኒስትሩ የብልጽግና አባላትንና የሚመለከታቸውን ክፍሎች ሰብስበው ስለ ጉዳዩ ሲገልፁ ብዙዎቹ ተገርመው ነበር። በተለይ ስለወደብ አስፈላጊነት የሰጡትን ትንታኔ ምንም ዓይኑን ሳያሽ ያመነው ዜጋ ቁጥር ቀላል አልነበረም። በርግጥም ጉዳዩ ዓይን የሚያሳሽ አልነበረም።

> **በእርግጥም የሁሉም አቧራ አስነሺዎች ሁኔታ እዚህ ግባ የሚባል ዓይነት አይደለም። በርግጠኛውና በተጨባጩ ዓለም ወደቡ መልማቱ ላይቀር የነሱ እንዲህ መሆን ምን ይሉታል?። አቧራ ያነሱት ሰዎች ሀሳብ የኢትዮጵያንና የኢትዮጵያውያንን ነገን ማየት ያልቻለ ፤በንጋት መንገድ ላይ መቆሟን ያላስተዋሉ ናቸው**

በጉዳዩ ላይ ያደረጉት ገለጣ ከወደብ አስፈላጊነት ባሻገር፣ አማራጭ አስተማማኝ የወደብ አገልግሎት ለማግኘት እንደ ሀገር የሚደረገው ጥረት ሰጥቶ በመቀበል፣ አብሮ በመለወጥ መርሕ የተገዛ መሆኑ፤ ዜጎች በጉዳዩ ላይ ወጥ የሆነ አቋም እንዲይዙ አድርጓል።

በተለይ ያለ ወደብ መኖራችን ልክ ጂኦግራፊያዊ እስር ቤት /geographical prison/ ውስጥ እንዳለን ከማስመሰሉ ጋር አያይዘው፤ ወደብ ለኢትዮጵያውያኖች ግድ ስለማለቱ ጉዳይ ያነሱት ለብዙዎቻችን አሳማኝ ነበር። አንድ ቀን መነሳቱ አይቀርም እያልን በየልቦናችን የምንጠብቀውና የምንፈልገውም በመሆኑ ሁላችንም ጆሯችንን የሰጠነው ስለመሆኑ መሸሽግ አይቻልም።

ይሄንን ሳይንሳዊ ትንታኔና ታሪካዊ ዳራ የተንተራሰ የጠቅላይ ሚኒስትሩን ገለፃ በመገናኛ ብዙኃን የተከታተለ ሁሉ መገረሙ አልቀረም። ጠቅላይ ሚኒስትሩ “ምን ሆነው ነው ግብዓተ መቃብሩ ከ30 ዓመት በፊት የተፈፀመውን ይሄን የወደብ ጉዳይ ዳግም በማንሳት የሕዝቡን ቁጭት መቀስቀስ የፈለጉት?” በሚል የታዘቡ መኖራቸውም አልቀረም።

ከዚሁ ትዝብት ጋር ተያይዞ የጠቅላይ ሚኒስትሩ ገለፃ ከበስተጀርባው አንዳች ሽፍጥ ያለው ስለመኖሩ የጠረጠሩና በሽሙጥ ዓይናቸው አይተው የሸረደዱትም ወገኖች አልጠፉም። እነዚህ በተለይ ጠቅላይ ሚኒስትሩ ስለወደብ አስፈላጊነት የሰጡትን እውነታ አዘል ትንታኔ ሳይቀር ሽምጥጥ አድርገው ጠቀሜታውን ከደዋል።

እንዳውም “መንግሥት አሁን በተጨባጭ በኢትዮጵያ ውስጥ የገጠመውን አንዳንድ ተቃውሞና ወቅታዊ እውነታ ለመሸፈን የተጠቀመበት ዘዴ ነው” ሲሉም መላ ምታዊና ግላዊ ግምታቸውን ከየኪሳቸው እያወጡ የሰነዘሩ ነበሩ።

ያም ሆነ ይህ በማይታመን ፍጥነት ሀገራችን በወደብ ጉዳይ ከሶማሌ ላንድ ጋር የመግባቢያ ስምምነት መፈራረሟ ተሰማ። አስደማሚው ፊርማ በርበራ ወደብን ለመጠቀም የ50 ዓመት ውልን ማሰሩም ተበሰረ። በነገራችን ላይ ውሉ ከዚህም በላይ ሊራዘም መቻሉ ታሳቢ መሆኑ እንደተጠበቀ ነው።

ዞሮ ዞሮ ይህ ከአዲስ አበባዋ ፒያሳ ተነስቶ እስከ ዱከም እንደውም እስከ ደብረ ዘይት መዳረሻ የሚዘልቀው የ20 ኪሎ ሜትር የሊዝ ኮንትራት ውል መታሰሩ ተረጋገጠ። ይሄ ከ90 በመቶ ለሆኑ ኢትዮጵያውያኖች የምሥራች ነው። ብዙዎች ደስታቸውን ሲገልፁ ተደምጠዋል። ፌሽታም አድርገዋል።

ሐርጌሳን መዲናዋ ያደረገችውን ሶማሌ ላንድ ጨምሮ ምሥራቁን የሀገሪቱን ክፍሎች ማልማቱ በተለይ ድሬዳዋን የምሥራቅ አፍሪካ የኢንዱስትሪ ከተማ ማድረጉን ምሑራን ተነተኑ። እስከ በርበራ የሚዘልቀው የፈጣን የባቡር መስመር ዕውን ሊሆን እንደሚችልም ተነበዩ። ትንቢቱ በሁለት ዓመት ጊዜ ውስጥ በተግባር ተፈፅሞ የመታየቱን አይቀሬነትም እየተነገረ ነው።

ስምምነቱ ተጎራባች ሀገራቱን ከጉርብትና ባሻገር በልማትም እርስ በእርስ የሚያስተሳስርና ሕዝቦቻቸውን ተጠቃሚ የሚያደርግ መሆኑንም አነሱ። ኢትዮጵያ ላለፉት 30 ዓመታት በተሳሳተ ፖሊሲና ስትከተል በቆየችው ከዚሁ ጋር የተወዛገበ የፖለቲካ አቅጣጫ ያጣችውን ወደብ በመጠቀም ልማቷን ማፋጠን እንደምትችል ሲገልፁ ሰነበቱ።

ሀገሪቱ ወደፊት ኢኮኖሚዋ እያደገ ሲሄድ በአካባቢው የሚገኙ ወደቦችን የመጠቀም አቅሟ እየጨመረ መሄዱ አይቀርም። እንደ ሶማሌ ላንዱ ወደብ ሁሉ ከጎረቤት ሀገሮች ጋር እጅ ለእጅ ተያይዘው በጋራ መልማት የሚችሉባቸው ሰፊ ዕድሎች አሉ። የነዚህ ሁሉ ይፋ መሆን ከወደቡ ተጠቃሚነት ፊርማ ጋር ተያይዞ በጠቅላይ ሚኒስትሩ ገለፃ መባነን የጀመረው አቧራ ይበልጥ ተነሳ።

እዛም እዚህም በተፈጠሩ ግላዊ መላምቶችና ግምቶች ታጅቦ የባሰውኑ መቡነኑን ተያያዘው። በዜግነት “ኢትዮጵያዊ ነን” ብለው ወገባቸውን ይዘው የሚሞግቱ ግን በተግባር ኢትዮጵያዊነታቸው ጠብ ሲል የማይታይ ኢትዮጵያዊ ተብዬዎች ሁሉ አቧራ በማስነሳቱ ጎራ ታደሙ።

የሞቃዲሾዋ ሶማሌ “ለጊዜው ከሶማሌ ላንድ ጋር ብንለያይም አንድ ሀገርና አንድ ሕዝብ ነን” የሚል የያገባኛል ቅሬታ አነሳች። ይሄንኑ የኢትዮጵያ ታሪካዊ ጠላት ግብፅ ሳትቀር ከነዚሁ አቧራ አስነሺዎች ጎራ ተሰልፋና ከስድስት በላይ ቦታ እንደተከፋፈለች ለሚነገርላት የሞቃዲሾዋ ሶማሌ ተቆርቋሪ መስላም የቅሬታ ድምጿን አሰማች። እንዳውም ተቃውሞውን በግንባር ቀደምትነት በመምራት የጎላ ተሳትፎ በማድረግ የተነሳውን አቧራ የበለጠ አጨሰችው።

ግብፅንም ሆነ የሞቃዲሾን ሶማሌ እንደዚሁም በግብር ኢትዮጵያዊነት የማይንጸባረቅባቸውን ኢትዮጵያዊ ነን ባይ የዚህ የተቀደሰ የወደብ ተጠቃሚነት ጉዳይ ከዓላማው በራቀ መንገድ ከአቅሙ በላይ አጯጯሁት። ከጎረቤቷ ኢትዮጵያ ጋር በጋራ መልማት ላይ ልቧ የተንጠለጠለው ሶማሌ ላንድም በፍጹም ጆሮዋን አልሰጠቻቸውም ።

በእርግጥም የሁሉም አቧራ አስነሺዎች ሁኔታ እዚህ ግባ የሚባል ዓይነት አይደለም። በርግጠኛውና በተጨባጩ ዓለም ወደቡ መልማቱ ላይቀር የነሱ እንዲህ መሆን ምን ይሉታል?። አቧራ ያነሱት ሰዎች ሀሳብ የኢትዮጵያንና የኢትዮጵያውያንን ነገን ማየት ያልቻለ ፤በንጋት መንገድ ላይ መቆሟን ያላስተዋሉ ናቸው። ኢትዮጵያ እና ሕዝቦቿ ይህንን ቀን መሻገራቸው፤ወደቡም መልማቱ የማይቀር ነው። መንጋቱ ላይቀር ይሉኋል ይኸው ነው !።

# ከቀጣናዊ እስከ ዓለምአቀፍ ትስስር

ቴልጌልቴልፌልሶር (የኩሽ አሽከታብ)

ወቅታዊና ሰሞነኛ ከሆኑ ኢትዮጵያዊ ጉዳዮች ውስጥ አንዱ የባሕር በር ነው:: እንደ አንድ ሰፊና ነፃ ሀገር የባሕር በር ጥያቄን ስናነሳ በብዙ ሀገራዊና አፍሪካዊ ምክንያቶች ታጅበን ነው:: ከምክንያቶቻችን ጥቂቶቹን ብንገልጽ እንኳን ከቀጣናዊ ጉርብትና ጀምሮ እስከ ዓለምአቀፉ የንግድና የኢኮኖሚ ትስስር ድረስ ያለውን ይይዛል:: ለተረዱን ዓላማችን አንድና አንድ ኅብረ - ውህድ የበረታበት ቀጣናዊ አብሮ የመልማት ዓላማ ነው::

እንደሀገር የመጀመሪያው ዓላማ ኢትዮጵያ እንድትጠቀም ማድረግ ነው። ኢትዮጵያ ትጠቀም ስንል ግን ሌላውን ሀገርና ሕዝብ ጎድተን አይደለም:: ኢትዮጵያን የምንጠቅምበት ሂደትም ያለንን በመስጠት፣ የሌለንን ደግሞ በመቀበል ነው:: ይሄ ሂደት በቀጣናው ያሉ ሀገራትን ከማስተሳሰር ጀምሮ፣ አፍሪካን አንድ ወደማድረግና በዓለምአቀፍ ደረጃም የላቀ ሚናን ከመወጣት አንጻር የሚሰላ ነው::

ሌላው የባሕር በር ጥያቄአችንንም ሆነ ሌሎች የሁለትዮሽ የጋራ ጉዳዮችን በተመለከተ ሁላችንንም የሚያግባባው እውነት የኢኮኖሚ፣ የፖለቲካ፣ የዲፕሎማሲና የጉርብትና ትስስሮች በአንድ ሀገር የበላይነትና የብቻ ፍላጎት ነፀብራቅ የሚሆኑ አለመሆናቸው ነው:: ይሄ ማለት ሁሉን አካታች የጋራ መር የሆነ ውይይትና ተግባቦትን ይሻል::

እኚህ ሂደቶች በሰጥቶ መቀበል መርህ፣ በመነጋገርና በመግባባት ጽንሰ ሃሳብ፤ ከሁሉ በላይ ደግሞ አብሮ በማደግ መርህ ሁሉን አቃፊ በሆነ ሥርዓት የሚመሩ ናቸው:: እውነታው ይሄና ይሄ ከሆነ፤ ጥያቄአችን በየትኛውም መልኩ ቢታይ ፍትሐዊ ነው ማለት ይቻላል:: ከታሪክ አኳያ ቢቃኝም ጥያቄአችን ነውር ያለው አይደለም::

ከቀይ ባሕር ጋር የነበረንን የበላይነት ለማየት በዓለም ላይ አራት ከሚሆኑ የወቅቱ ገናና እና ሥልጡን ሀገራት አንዱ እንደሆንን የአክሱም ሥልጣኔን ማስታወሱ ብቻ በቂ ነው:: ከተፈጥሮ አንጻር ደግሞ ቀይ ባሕርና ኢትዮጵያ በጥቂት ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ እየተያዩ ያሉ እንደሆኑ መረዳት ይቻላል::

እንደሀገር የጥያቄአችን ትልቁ ዓላማ ‹ሁሉን አቃፊነት፣ የአብሮ ማደግ መርህ› ነው:: በባሕር በር በኩል በኢኮኖሚም ሆነ በፖለቲካ በሌሎች የእርስ በርስ ግንኙነቶች በኩል ተጠቅመን ሌሎችን ለመጥቀም ያነሳነው የይገባኛል ጥያቄ እንጂ ማንንም ለመጉዳት አስበን ያደረግነው አይደለም::

ለብዙ አፍሪካውያን የነፃነት ትግል አቅም የነበረች ሀገር እና ሕዝብ፤ በምንም ዓይነት ሚዛን ሌሎችን የምትጎዳበት የሞራል ልዕልና የላትም:: በባሕር በር ጥያቄአችንም ሆነ በሌሎች አፍሪካዊ ጉዳዮቻችን ላይ ትልቁ ዓላማ አብሮ ሠርቶ አብሮ ማደግ የሚል ነው:: ከጥቂት ለሀገራችን በጎ የማይሹ ሀገራት በስተቀር ይሄንን ፍላጎታችንን ብዙዎች ይረዱታል::

አንዳንድ ሀገራት በወቅታዊው ሁኔታ ምቹ አጋጣሚ ያገኙ መስሏቸው ተገቢ ጥያቄአችንን ተገቢ እንዳይደለ በማናፈስ ታሪካዊ ትስስራ ችንን ለማላላት ይሞክራሉ:: በይገባኛል ስም ያነሳነውን የባሕር በር ጥያቄ ታሪክ ነጋሪና ተፈጥሮን ዘካሪ ከሆኑ ጥያቄዎች ሁሉ ምርጡ ጥያቄ ነው:: ምርጥነቱን የሚያጎላው ደግሞ ከሕዝብ የዕለት ተዕለት የፍላጎት መናር ተነስተን የተፈጥሮ ሀብታችንን ለጋራ ዓላማ በጋራ እንጠቀም የሚል የእሳቤ መሠረት ላይ የታነጸ መሆኑ ነው። ከጎረቤቶቻችን ጋር የነበረንን ትስስር ከማሳደግና ከሌሎች ሀገራት ጋር አዲስ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ጉርብትናን ከመፍጠር አኳያ የላቀ ስለሆነ ነው::

> **ዓለም ወደ አንድ መንደር እየመጣች ባለችበት በዚህ ጊዜ፣ ሀገራት አብሮ በፍቅር ተያይዞ ከማደግ ውጪ ምርጫ በሌላቸው በዚህ የትስስር ወቅት፤ አብረን እንልማ፤ አብረን እንደግ የሚለው የኢትዮጵያ ጥያቄ እንግዳ ጥያቄ ሊሆን አይገባም**

ዓለም ወደ አንድ መንደር እየመጣች ባለችበት በዚህ ጊዜ፣ ሀገራት አብሮ በፍቅር ተያይዞ ከማደግ ውጪ ምርጫ በሌላቸው በዚህ የትስስር ወቅት፤ አብረን እንልማ፤ አብረን እንደግ የሚለው የኢትዮጵያ ጥያቄ እንግዳ ጥያቄ ሊሆን አይገባም፤ ከሱማሌ ላንድ ጋር የተደረገውም የሁለትዮሽ የመግባቢያ ሰነድ ስምምነት የዚሁ እውነታ አካል ነው::

ቀጣዩ እንቅስቃሴ እንደ መነሻችን አብሮነትን ያቀፈ፣ ከአፍሪካ ቀንድ ጀምሮ ዓለም አቀፋዊነትን የዋጀ ነው:: እንዲህ ላለው አብሮ ሠርቶ አብሮ ማደግን እንደመርህ ለያዘ አፍሪካዊ ዓላማ ሁሉን አግባቢ አቀራራቢና አስታራቂ ሃሳቦች እንጂ ጎራ ለይቶ የማይሆን ቃላትን መለዋወጥ ለማንም የማይጠቅም ድርጊት ነው።

ኢትዮጵያና ሶማሊያ ጎረቤት ሀገራት ብቻ ሳይሆኑ፤ ታሪክ አብሮ የገመዳቸው፣ ባህል፣ ልማድ፣ ታሪክ የተወራረሱ ሀገራት ናቸው:: ይሄን በመሰለው ሁኔታ በባሕር በር ጥያቄአችን ታሪካችን ይጠነከራል እንጂ አይላላም። ስምምነቱ የሁለቱን ሀገራት የንግድ እና የአጋርነት መንገድ የሚያሳልጥ እንጂ በማንም ሉአላዊነትና የአንድነት ግዛት ላይ አደጋ የሚጥል አይደለም::

ከማስታረቅና ከማግባባት ውጪ እኩይ ዓላማ ይዘው የቆሙ ሀገራት የቀጣናውን ሰላምና መረጋጋት፣ እድገትና ጉርብትና የማይፈልጉ ስለመሆናቸው ለማወቅ ጠቢብ መሆን አይጠይቅም:: እነኚህ ሀገራት የባሕር በር ጥያቄአችንን ዓላማ በሚገባ የተረዱ ቢሆንም በተጻራሪው ለመቆም ተገደዋል::

በዚህ ሁሉ መሀል ግን በላቀ የተግባቦት መንፈስ፣ በበረታ የውይይት መድረክ ሀገራችን ኢትዮጵያ ቀጣናዊ ትስስርን በመፍጠር ከሁሉም ጋር በሰላም ከመኖር ጋር በትብብር ለመሥራት እየጣረች ትገኛለች:: ውጥረትን ከሚፈጥሩና ከሚያባብሱ መግለጫዎች ታቅባ ሁኔታዎችን እንደየ ባህሪያቸው እያስተናገደች ትገኛለች::

በርግጥ ችግሮችን መፍታት የሚቻለው እዚያና እዚህ ሆኖ ቃላት መለዋወጥ ሳይሆን፣ ቀረብ ብሎ መነጋገር ነው:: አሁን ባለው ሂደት የባሕር በር ጥያቄአችን ምላሽ እንዲያገኝ በሁሉም ረገድ የዓላማውን አስፈላጊነትና የአብሮ ማደግ መርሁን ሁሉም እንዲረዱት የዲፕሎማሲ ሥራ ያስፈልጋል::

ይሄን አቅጣጫ በተመለከተ በርካታ ባለሙያዎች የጋራ መግባባት አላቸው:: ለአብነት ያክል ከኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ጋር ቆይታ ያደረጉት በአሜሪካ የኢትዮጵያ ባለሙሉ ሥልጣን አምባሳደር ኢንጂነር ስለሺ በቀለ (ዶ/ር) ‹ኢትዮጵያ በተገቢው ዲፕሎማሲና የሰጥቶ መቀበል መርህ የባሕር በር የማግኘት ሙሉ መብት አላት› ሲሉ ተደምጠዋል::

‹እንደ ኢትዮጵያ ሰፊ ሕዝብ ከሰፊ ፍላጎት ጋር ይዛ የባሕር በር የሌላት ሀገር በዓለም እንደሌለ አስታውሰው፤ በቀጣዮቹ አምስትና ስድስት አመታት ውስጥ የኢትዮጵያ ሕዝብ 150 ሚሊዮን እንደሚደርስና ይሄም በዓለም ላይ ብዙ ሕዝብ ካላቸው ሀገራት ውስጥ ከፊት እንደሚያስቀምጣት በመጠቆም የባሕር በር ጉዳይን ከህልውና ጥያቄ ጋር መሳ ለመሳ አቁመውታል:: ይሄን መሰል የሕዝብ ቁጥርና ፍላጎት የሚስተናገደው ደግሞ እንደባሕር በር ባሉ ኢኮኖሚያዊ ፋይዳቸው ላቅ ባሉ ጉዳዮች በኩል እንደሆነ መስክረዋል::

ከአምባሳደሩ ንግግር ብንነሳ የባሕር በር ለእኛ ለኢትዮጵያውያን ትርጉሙ ዘርፈ ብዙ ነው:: ከኢኮኖሚ ተጠቃሚነት ባለፈ ገመናችንን የምንጠብቅበት፣ የደህንነት ዋስትናችንን የምናረጋግጥበት፣ እንደሀገር እየጨመረ ለመጣው ለሕዝብ ቁጥራችን ደግሞ ተመጣጣኝ የፍላጎት ምላሽ የሚሰጥ እፎይ ማያ ነው:: ይሄን ዘርፈ ብዙ ዋጋ ያለው ጥያቄ ሰላም ተኮር በሆነ ውይይትና የዲፕሎማሲ እርምጃ ካልሆነ በእኛም ሆነ በሌላው ወገን በኃይል ትንቅንቅ የማይሞከር ነው::

ወቅታዊውን የኢትዮጵያና የሱማሌላንድ ስምምነት ተከትሎ የመጣውን እሰጣ አገባ በተመለከተም «ካነሳነው ጥያቄ ጋር በተቃራኒ የቆሙም ሆኑ የሚቆሙ ሀገራት ኢትዮጵያ ወደብ በማግኘቷ ተጎድተው አሊያም የሚጎዳ አካል ኖሮ ሳይሆን እድገትና መጻኢ ንቃታችንን በበጎ ካለመመልከት የመጣ ነው» ብለዋል። ይሄ የአምባሳደሩ መልዕክት ከይገባኛል ጥያቄአችንም ሆነ ከሌሎች ቀጣናዊ መሻቶች ጋር አሁን ያለንበትን ሁኔታ በግልጽ የሚያስረዳ እውነታ ሆኖ የሚቃኝ ነው::

ማንንም የሚጎዳ አእምሮና ልብ የለንም። ብዙዎችን አስጠልለን ቀን ያወጣን የታሪክ ፊተኞች፣ ከእኔነት የበቀለ ራስወዳድነት ያልጎበኘን የፍትህ ሚዛኖች ነን:: ማንም በሚዛናችን ፊት አንሶና ተጨቁኖ ማየትን አንወድም:: በዚህ ሁሉ ብርቱነታችን ውስጥ ደግሞ ለማንም ጥቅሙን አሳልፎ የማይሰጥ፣ ማንንም የማይፈራና ስለሀገርና ሕዝብ ወደ ኋላ የማያፈገፍግ ወኔ የታደልንም ነን:: ሁላችንንም የሚያግባባ፣አግባብቶም ወደአብሮ መሥራት የሚወስደን መርህ ሰጥቶ መቀበል የሚለው መርህ ነው::

ከጥንት እስከዛሬ ፍላጎቶቻችን ማንንም ጎድተው አያውቁም:: የመጪው ጊዜ እድገትና ተጽእኖ ፈጣሪነታችን አስግቷቸው እንጂ በየትኛውም ዘመን ላይ ያነሳነው ጥያቄ የቀጣናውን ሀገራት ጎድቶ አያውቅም። በውይይት እና በተግባቦት በአጭር ማለቅ የሚችለውን ጥያቄ ነው እሰጣ አገባ ውስጥ እንዲገባ በማድረግ ቀጥተኛውን መንገድ የሚያጠማዝዙት::

ለየትኛውም አብሮ የማደግ ጥያቄም ሆነ የሁለትዮሽ ጉዳይ ዲፕሎማሲያዊ አካሄድ የላቀ ዋጋ አለው:: እዛም እዚህም የሚሰሙ፣ ለማንም ክብር የማይጨምሩ ቃላቶች ቀጣናውን የጦር አውድማ ከማድረግ ባለፈ ትርፍ የለሽ ስለሆኑ፤ ጉዳዮቻችን ወደጠረጴዛ እንዲወርዱና እንድንጨባበጥባቸው ማድረግ ቀሪ የቤት ሥራችን ይሆናል::

ታላቁን የሕዳሴ ግድብ በላቀ የዲፕሎማሲ ጥረት ከትንሳኤው እንዳደረስነው ቀጣይ ሂደቶቻችንም በዚያ መልኩ መቃኘት አለባቸው። ዓላማው ሰጥቶ መቀበልና ተቀብሎ መስጠት የሆነ ሀገር፤ በማንም ላይ ጫና ለማድረስ ሞራሉ አይፈቅድለትም። የዚህ ሞራል ባለቤት ከሆኑት ውስጥ ደግሞ እኛ ኢትዮጵያውያን ቀዳሚዎቹ ነን:: ማንንም ሳንጎዳና ማንም እንዲጎዳን ሳንፈቅድ እንደመጣንበት የአብሮ ማደግ ትናንትና ወደ ነገ ለመሄድ መቁረጥ ጥያቄአችንን እውን ከሚያደርጉ ሂደቶች አንዱ ነው::

እንደ አንድ ትልቅና ሰፊ ሀገር የሕዝባችንን ህልውና ለማስቀጠልም ሆነ መጻኢ ገናናነታችንን ለመቀበል የባሕር በር ያስፈልገናል:: በሕዝብ ቁጥሯም ሆነ በፍላጎት መናር፣ በኢኮኖሚ ግስጋሴም ሆነ በቀጣናዊ ሰላም ማስጠበቅ ሀገራችን ኢትዮጵያ የባሕር በር ያስፈልጋታል:: አሁን ያለችውም ሆነች ወደፊት የምትፈጠረው ሀገራችን በዚህ የሕዝብ ጥያቄ ውስጥ ስታልፍ ነው ትንሳኤዎቿ እውን የሚሆኑት::

በተያይዞ ማደግ ዓላማችን የገባቸው በባሕር በር ጥያቄአችን ላይ ጠጠር በማዋጣት አብረውን ይቆማሉ:: ይሄ አሁን ላለው መንግሥትና ለትውልዱ ኢትዮጵያን የመታደጊያና የማዋለጃ መርህ ነው::

# የማቲዎስ ምትክ ቤተሰቦችን ማፍራት የቻለው የ20 አመት ተቋም

**ሰሚራ በርሀ**

የመረዳዳትና ለተቸገሩ ሰዎች የመድረስ ባህል ኢትዮጵያውያን ከሚታወቁባቸው መገለጫዎቻቸው መካከል አንዱ ነው፡፡ ይህ ባህል ከራስ አልፎ ለሌሎች ተስፋ መሆን የቻሉ ተቋማት እንዲገነቡ እያደረገም ነው፡፡ እነዚህ ተቋማትም መነሻቸው ለሌሎች መትረፍ ነውና በትጋትና በለውጥ ዓመታትን እየተሻገሩ ይገኛሉ፡፡ «የማቲዎስ ወንዱ የኢትዮጵያ ካንሰር ሶሳይቲ» ምግባረ ሰናይ ተግባርም የዚሁ ማሳያ ነው፡፡

የማቴዎስ ወንዱ መስራቾች አቶ ወንዱ በቀለ እና ወ/ሮ አምሳለ በየነ በተለያየ የሥራ መስክ ላይ ተሰማርተው የሚሠሩ በጥሩ የኑሮ ደረጃ ላይ የሚገኙ እና በሁለት ልጆች ተወስነው ይኖሩ ነበር፡፡

ይህን ኑሯቸውንና የልጆቻቸውን ሁለት ብቻ መሆን የተመለከቱ የቅርብ ወዳጆቻቸው ሦስተኛ ልጅ እንደሚጨምሩ በተደጋጋሚ ወተወቷቸው፤ እነአቶ ወንዱ ግን «ያሉን ይበቁናል» ብለው ተቀመጡ፤ ይሁንና ውትወታው በዛና ልባቸውን አሸፈተው፤ ሁለተኛ ሴት ልጃቸውን ከወለዱ ከ10 አመት በኋላ አዲስ የቤተሰብ አባል ተቀበሉ፡፡

ከእርግዝናው ጊዜ ጀምሮ በብዙ ጉጉት እና ናፍቆት ተጠብቆ የመጣው ሕፃንም ማቲዎስ ተባለ፡፡ ማቲዎስ የቤተሰቡን ደስታ ጨመረው፡፡ ወላጆችም ለማቲዎስ ትኩረት ሰጥተው ሕይወታቸውን በደስታ መምራት ጀመሩ፡፡

ማቲዎስ የሁለተኛ አመት የልደት በዓሉን ለየት ባለ መልኩ ካከበረ በኋላ ግን ወላጆች ልጃቸው ላይ አዲስ ነገር ማስተዋል ጀመሩ፡፡ «እኔና ባለቤቴ በጣም በመጓጓታችን ትኩረት አደረግንበት መሰለኝ የሁለተኛ አመት ልደቱን ያከበርነው እጅግ ብዙ ሰው በተሰበሰበበት ነበር» ሲሉ የማቲዎስ አባት ያስታውሳሉ፡፡

ሕፃን ማቲዎስ ላይ የህመም ምልክት ሲያስተውሉ ለሕክምና አቅራቢያቸው ወደሚገኝ ሆስፒታል አቀኑ፤ ሕፃን ማቲዎስ ላይ የተለየ ነገር የተመለከተው ሐኪም፣ ለሌላ ሕክምና ወደ ጥቁር አንበሳ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል መሯቸው፡፡ ልጃቸው በደም ካንሰር ህመም መጠቃቱን የማቲዎስ ወላጆች ሰሙ፡፡

«በአንድ ወቅት በመሥሪያ ቤቴ በካንሰር ታሞ የሞተ ወጣት አውቃለሁ፤ ከዚያ ውጪ ግን በፍጹም ስለ ካንሰር የማውቀው አልነበረም» የሚሉት አቶ ወንዱ፣ በጊዜው እሳቸውም ሆኑ ባለቤታቸው በተፈጠረው ነገር ፍጹም መደንገጣቸውን ያስታውሳሉ፡፡ ቀጣዩ አማራጭ ክትትላቸውን በጥቁር አንበሳ ሆስፒታል ማድረግ ሆነ፡፡


የካንሰር ሕክምና ለታካሚውም ሆነ ለአስታማሚው እጅግ በጣም ፈታኝ መሆኑን የሚያናገሩት አቶ ወንዱ፣ በሆስፒታሉ ለካንሰር ህሙማን ታካሚዎች ያለው ቦታ ምቹ አለመሆን፣ የምርመራ መሣሪያዎች በበቂ ሁኔታ አለመገኘት፣ መድኃኒቶችን በፍጥነት ለማግኘት መቸገር የሕክምና ክትትል ሂደቱን ከባድ አደረጉት፡፡

የጥቁር አንበሳ ሆስፒታል ከሁሉም የሀገሪቱ ክፍሎች የሚመጡ ህሙማን የሚታከሙበት በመሆኑ አንዳንዴ ህሙማን በጊዜያዊ መቆያ ክፍል ኮሪደር አግዳሚ ወንበር ላይ ለመተኛት ይገደዳሉ፡፡ በሆስፒታሉ ውስጥ ለካንሰር ታማሚዎች ተብሎ የተለየ የማቆያ ቦታ የለም፡፡ በካንሰር የተያዙ ሰዎች ደግሞ በሽታን የመከላከል አቅማቸው ስለሚዳከም በተለያየ ኢንፌክሽን የሚያዙበት ሁኔታ ሰፊ በመሆኑ ለማገገምና ለመዳን ጊዜ ይወስድባቸዋል፡፡

አቶ ወንዱ እና ቤተሰቦቻቸው ለልጃቸው ማቲዎስ የሚታዘዘውን መድኃኒት በቀላሉ የማግኘት ዕድል ስለነበራቸው በሆስፒታሉ ለሚታከሙ ሰዎችም ይተርፉ እንደነበርም አቶ ወንዱ ይገልጻሉ፡፡ አቶ ወንዱ የልጃቸውን የሕክምና ሁኔታ አሜሪካ ከሚገኘው «ሴንት ጁድ» የተሰኘ የሕፃናት ሆስፒታል ጋር በኢ-ሜይል ግንኙነት በማድረግ በቅርበት ይከታተሉ ነበር፡፡ ሆስፒታሉም ከሚሰጠው ሕክምና በመነሳት ይድናል የሚል ተስፋ ነበራቸው፡፡

ሕፃን ማቲዎስ ለሁለት አመት ባደረገው ሕክምና ሰውነቱ ውስጥ የነበሩት የካንሠር ሴሎች መሞታቸው ተረጋግጦ ከዚያ በኋላ ይደረግ የነበረው ሕክምና የካንሰር ሴሎች ዳግም እንዳይከሰቱ የማረጋገጥ ሥራ ነበር፡፡ «የሕክምና ጊዜው ውጤታማ ነበር» የሚሉት አቶ ወንዱ፣ የመዳን ዕድሉ ተስፋ ሰጪ በነበረበት ሰዓት የካንሰር ሴሎች እንደገና በመከሰታቸው ወደ ውጭ እንዲታከም በሐኪሞች ቦርድ ተወሰነ» ሲሉ ይገልጻሉ፡፡

አቶ ወንዱ እና ቤተሰባቸው በሀገር ውስጡ ሕክምና የፋይናንስ አቅማቸው በመዳከሙ አማራጫቸው መኖሪያ ቤታቸውን መሸጥ ነበር፡፡ በቅርብ ሰዎቻቸው አማካኝነት ነፃ ሕክምና የሚያገኙበትን ዕድል አግኝተው የመሄጃ ቀናቸውን



ማቲዎስ በ20 ዓመታት

ሲጠባበቁ የጓጉለትን ልጃቸውን ማዳን ሳይችሉ ቀሩ፤ ሕፃኑ ማቲዎስ መስከረም 13 ቀን 1996 ዓ.ም ከዚህ ዓለም በሞት ተለየ፡፡

አቶ ወንዱ ልጃቸውን በሚያሳክሙበት ወቅት ሰዎች ስለ ካንሰር ህመም የተሳሳተ አመለካከት እንዳላቸው እና ከሕክምና ባለሙያዎች ገጽ ላይ ተስፋ አስቆራጭ መልዕክት አስተውለዋል፡፡ ከፍተኛ ገንዘብ እያወጡ ለልጃቸው መድኃኒት በሚገዙበት ጊዜም ሰዎች የመዳን ዕድሉ አናሳ መሆኑን በመጥቀስ ገንዘባቸውን እንዳያባክኑ ሊመክሯቸው ሞካክረዋል፡፡

«ማቲዎስን ለማሳከም የመጨረሻው ዕድል ድረስ ሞክረናል፤ ነገር ግን ፈጣሪ አልፈቀደውም» የሚሉት አቶ ወንዱ፣ ልጃቸውን የነጠቃቸውን ህመም የሌሎችን ሕይወት እንዳይነጥቅ የበኩላቸውን ለማድረግ፣ ሊድንና አስቀድሞ ሊከላከሉት በሚቻል ህመም ላይ ሰዎች የነበራቸውን «ካንሰር አይድንም» የሚል የተሳሳተ ግንዛቤ ማስተካከል እንደሚገባ ወሰኑ፡፡

አቶ ወንዱ «እኛ ለልጃችን ስለምንሰጠው የምግብ ዓይነት በምንጨነቅበት ሰዓት በሆስፒታሉ ግን ለልጆቻቸው በቂ ምግብና ሕክምናም መስጠት ያልቻሉ መኖራቸው በጉዳዩ ላይ እንደሠራበት አድርጎኛል» ይላሉ፡፡ እናም ልጃቸው ካረፈ ከስድስት ወራት በኋላ በልጃቸው ስም «የማቲዎስ ወንዱ የኢትዮጵያ ካንሰር ሶሳይቲ»ን ሚያዝያ ዘጠኝ ቀን 1996 ዓ.ም ከባለቤታቸውና ከሌሎች 13 ሰዎች ጋር በመሆን አቋቋሙ፡፡

አቶ ወንዱ የድርጅቱ ዋና ሥራ አስፈፃሚ፣ ባለቤታቸው ደግሞ ፀሐፊና ገንዘብ ያዥ ሆነው በልጆቻቸው አጋዥነት ለስድስት አመታት ያህል በራሳቸው መኖሪያ ቤት ሥራቸውን ቀጠሉ፡፡

እሳቸው እንዳሉት፤ ሶሳይቲው የተቋቋመበት ዓላማ በካንሰር ታማሚ ሕፃናት ላይ አተኩሮ መሥራት ሲሆን፣ በካንሰር ህመም ላይ የሚታየውን የተሳሳተ አመለካከት በመቀየር ኅብረተሰቡ ትክክለኛውን የካንሰር ምንነት፣ የመከላከያና መታከሚያ አማራጮቹን እንዲያውቅ ማድረግ፣ በሀገሪቱ የካንሰር ሕክምና ተሟልቶ የሚሰጥበትን አመቺ ሁኔታ መፍጠር፣ አቅሙ ለሌላቸው አስፈላጊውን የሞራልና ማቴሪያል ድጋፍ መስጠት፣ የካንሰር ሕክምና ተሟልቶ የሚሰጥበትና ምርምርና ስርፀት የሚካሄድበት የካንሰር ኢንስቲትዩት እንዲቋቋም መርዳትና የሀገሪቱ የሕክምናና የትምህርት ተቋማት በካንሰር ላይ ምርምር እንዲያደርጉ ማበረታታት የሚሉት ናቸው፡፡

ሶሳይቲው በአሁኑ ወቅት 30 ቋሚ ሠራተኞች አሉት፣ በስምንት ፕሮጀክቶች ላይም አተኩሮ ይሠራል፡፡ ከፕሮጀክቶቹ አንዱ የካንሰር ህሙማንን እና ቤተሰባቸውን መርዳት ነው፡፡ የካንሰር ሕክምና በሀገሪቱ በሁሉም ቦታዎች ተደራሽ ባለመሆኑ ምክንያት ሕክምናውን ለማግኘት በርካታ

> **በቤተሰብ ውስጥ የተፈጠረን አንድ አሳዛኝ አጋጣሚ ወደ መልካም ነገር በመቀየር የተቋቋመው የማቲዎስ ወንዱ የኢትዮጵያ ካንሰር ሶሳይቲ የሚሠራቸውን ሥራዎች በማሳደግ በአሁኑ ሰዓት ጤናማ አፍሪካ የሚል ትልቅ ፕሮጀክት ቀርጾ እውን ለማድረግ እየሠራ ይገኛል**

ታካሚዎች ወደ አዲስ አበባ ይመጣሉ፡፡

ሶሳይቲው ለአስታማሚዎች ማረፊያ በማዘጋጀትና በመስጠት፣ ለታካሚዎች የሚታዘዝላቸውን እና ማግኘት ያልቻሉትን መድኃኒት በመግዛት፣ የላቦራቶሪ ምርመራዎችን በማሰራት፣ በቀን አራት ጊዜ የሚመገቡትን ተቋሙ አዘጋጅቶ በማቅረብ አገልግሎት ይሰጣል፡፡ በሶሳይቲው አርፈው ሕክምናቸውን ለሚከታተሉ ታካሚዎች ደግሞ ወደ ሆስፒታል ወስዶ የሚመልስ የትራንስፖርት አገልግሎት ይሰጣል፡፡ በአሁኑ ወቅትም ይህን አገልግሎት 154 ለሚሆኑ የካንሰር ህሙማንና ቤተሰቦቻቸው እየሰጠ ይገኛል፡፡

ተላላፊ ስላልሆኑ በሽታዎች ግንዛቤ ለመፍጠር ትኩረት አድርጎ የሚሠራባቸው ፕሮጀክቶችም አሉት፡፡ የመጀመሪያው ፕሮጀክት በሕፃናት ካንሰር ላይ ትኩረቱን ያደረገ ሲሆን፣ በካንሰር የተጠቁ ሕፃናትን ቤተሰቦች በማገዝ የሕክምና ሂደታቸውን ይከታተላል፤ ለጥቁር አንበሳ ሆስፒታል የካንሰር የሕክምና ክፍል ድጋፍ ያደርጋል፡፡

ከሌሎች ተቋማት ጋር ባደረገው ጥናት በኢትዮጵያ ተላላፊ ባልሆኑ በሽታዎች ምክንያት የሚጠቁ እና ሕይወታቸው የሚያልፍ ሰዎች ቁጥር በአጠቃላይ በሀገሪቱ ከሚከሰተው ሞት 52 በመቶ የሚሆነውን ድርሻ እንደሚይዝ ማወቅ ተችሏል፡፡

ከኢትዮጵያ ካንሰር አሶሲዬሽን፣ ከኢትዮጵያ ኩላሊት ህመም ማኅበር፣ ከኢትዮጵያ ስኳር ህመም ማኅበር እና ከኢትዮጵያ የልብ ህመም ማኅበር ጋር የኢትዮጵያ ተላላፊ ያልሆኑ ህመሞች ማኅበርን አቋቁሟል፡፡ ኅብረቱም በህመሞቹ ላይ የሚካሄዱ ጥናትና ምርምሮችን ያግዛል፡፡ የማህጸን በር ጫፍ ካንሰር እና የጡት ካንሰር፣ የትምባሆ ስርጭትን ለመቆጣጠር፣ የሳንባ ካንሰር ቁጥጥርና ስርጭትን ለመግታትና ተላላፊ ያልሆኑ በሽታዎችን አስቀድሞ ለመከላከል የአመጋገብ ሥርዓትን እና የአኗኗር ዘይቤን ማስተካከል በእጅጉ የሚረዳ ነው በማለት ሶሳይቲው ሰዎች የምግባቸውን ምንነት እንዲያውቁትና ጤናማ የአኗኗር ዘይቤዎችን እንዲከተሉ ይሠራል፡፡

ሶሳይቲው ከተመሠረተ 20 ዓመታት ያስቆጠረ ሲሆን፣ በነዚህ ዓመታትም በርካታ ሥራዎችን ሠርቷል፡፡ ከነዚህም ውስጥ ከ«ፒንክ ሪበን ሬድ ሪበን» (Pink Ribbon Red Rib-bon) ከተሰኘ ድርጅት ባገኘው የገንዘብ ድጋፍ ኢትዮጵያ ለመጀመሪያ ጊዜ ሀገር አቀፍ የካንሰር መከላከልና ቁጥጥር ዕቅድ እንዲኖራት አድርጓል፡፡ በሥራ ላይ የዋለው ይህ የብሔራዊ ካንሰር መቆጣጠሪያ እቅድ ትኩረቱን ያደረገው በጡትና ማህፀን በር ካንሰር ላይ ነው፡፡

ሶሳይቲው በሀገር ውስጥ ካሉ ስድስት ዩኒቨርሲቲዎችና ከ«አሜሪካ አካዳሚ ኦፍ ፔዲያትሪክስ» ባገኘው ድጋፍ የኢትዮጵያ ሕፃናትና ታዳጊዎች ካንሰር መቆጣጠሪያ እቅድ እንዲጸድቅ አስተዋጽኦ አድርጓል፡፡ በሚሠራው የትምባሆ ቁጥጥር ፕሮጀክት ሥራ በኢትዮጵያ የትምባሆ፣ አልኮልና የመድኃኒት ቁጥጥር አዋጅ እንዲጸድቅ ትልቅ አስተዋጽኦ አድርጓል፡፡

የማህፀን በር እና የጡት ካንሰር አስቀድሞ መከላከል እና በተወሰነ መልኩ ቅድመ ምርመራ ማድረግ የሚቻል በመሆኑ ሶሳይቲው የማኅበረሰቡን ግንዛቤ ከፍ ለማድረግ ያስችል ዘንድ የተለያዩ የግንዛቤ ማስጨበጫ እንቅስቃሴዎችን ሲያደርግ ቆይቷል፡፡ በአሁኑ ወቅት ስለ ጉዳዩ በሀገራችን ያለው መነሳሳት፣ ምርመራው በመንግሥት ጤና ጣቢያ ከሞላ ጎደል በነፃ እንዲሰጥ እና 14 አመት ለሆናቸው ሴቶች በሀገር አቀፍ ደረጃ ክትባት እንዲሰጥ መደረጉ ከዚሁ የተገኘ ውጤት ነው፡፡

የማቲዎስ ወንዱ የኢትዮጵያ ካንሰር ሶሳይቲ ከተለያዩ ዓለም አቀፍ ድርጅቶች ጋር በጥምረት ይሠራል፤ በካንሰር ዙሪያ ለሠራቸው ሥራዎች በሦስት አመት ውስጥ ብቻ አምስት ዓለምአቀፍ ሽልማቶችን አግኝቷል፡፡ በተለያዩ አህጉራት ካሉ ዓለምአቀፍ ተቋማት ጋርም ምክክር ማድረግ ችሏል፡፡

ሶሳይቲው በተለያዩ ጊዜያት ከጥቁር አንበሳ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል ጋር ተባብሮ በመሥራት የካንሰር ሕክምና ክፍሎችን የማደስ እና ዘመናዊ የመመርመሪያ መሣሪያዎችን የማስገባት ሥራዎችን የሠራ ሲሆን፣ በተለያዩ የሀገሪቱ ከተሞች ላይ ሰዎች በአቅራቢያቸው የካንሰር ምርመራ ማድረግ እንዲችሉ አድርጓል፡፡ በአሁኑ ወቅት ለታካሚዎች የሚውል የሕክምና እና ለሚሰጠው አገልግሎት ከሚያወጣው ወጪ ባሻገር ለመኖሪያ ቤት ብቻ በቀን እስከ አምስት ሺህ ብር፣ በወር 120 ሺህ ብር፣ በአመት ወደ ሁለት ሚሊዮን ብር የሚጠጋ ወጪ ያወጣል፡፡

ወይዘሮ ፀሐይ ተሾመ ሶሳይቲው ለካንሰር ህሙማንና ለቤተሰባቸው በሚያደርገው ድጋፍ ተጠቃሚ ሆነዋል፡፡ ወይዘሮ ፀሐይ በደሴ ከተማ የሚኖሩ ሲሆን፣ የመጀመሪያ ልጃቸውን ወልደው ሁለተኛ ልጅ ለመጨመር ሳይሳካላቸው ቀርቶ ከ28 አመታት በኋላ ሴት ልጅ ይወልዳሉ፡፡ «በፈጣሪ ፍቃድ አገኘኋት» የሚሏት ይህች ሁለተኛ ልጃቸው እስከ ሦስት አመቷ ድረስ በጥሩ ጤንነት ላይ ትገኝ ነበር፡፡

ነገር ግን የጤናዋ ሁኔታ እየተቀየረና አሳሳቢ እየሆነ መጣ። ከብዙ ፀሎት በኋላ ያገኟትን ልጃቸውን ይዘው በደሴ ከተማ የተለያዩ ምርመራዎችን እያደረጉ ከአንድ ወር በላይ ከቆዩ በኋላ በልጃቸው ሃይማኖት ኩላሊቷ ላይ የተከሰተው ዕጢ ወደ ካንሰር መቀየሩ ተነገራቸው። ለተሻለ ሕክምናም ወደ አዲስ አበባ ጥቁር አንበሳ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል ተላኩ፡፡

ወይዘሮ ፀሐይ ስለሆስፒታሉም ሆነ ስለሚያሳክሙበት ሁኔታ አስቀድመው የሰሙት መረጃ የሚያስፈራና ተስፋ አስቆራጭ ነበር፡፡ ወደ አዲስ አበባ እንደመጡም ልጃቸውን ለማሳከም የሚያርፉበት ቦታም ሆነ ዘመድ እንዲሁም የገንዘብ አቅምም አልነበራቸውም፡፡ ወይዘሮ ፀሐይ ሲወራ የሰሙትና መጥተው በአካል ያዩት አንድ እንዳልሆነ ይናገራሉ፡፡ ልጃቸው የኪሞቴራፒ ሕክምናውን በሆስፒታሉ ተኝታ ካደረገች ከአንድ ወር ከ15 ቀን በኋላ ቀሪውን ሕክምና ከቤታቸው እየተመላለሱ እንዲያደርጉ ተነገራቸው፡፡

ለወይዘሮ ፀሐይ ይህን ማድረግ ከባድ በመሆኑ የጤና ባለሙያዎች ከነገሯቸው በኋላ ወደ ማቲዎስ ወንዱ የኢትዮጵያ ካንሰር ሶሳይቲ መምጣት ቻሉ፡፡ «ወደ ማቲዎስ ወንዱ ከመጣው በኋላ ማረፊያ አገኘሁ፣ ለልጄ የሚያስፈልጋት መድኃኒት ተሟልቶልኝ፣ ትልቁን ጭንቀት አቅልለውልናል» በማለት በሶሳይቲው ስለሚያገኙት የአገልግሎት ጥራትና ስለተሰማቸው እፎይታ ይናገራሉ፡፡

በቤተሰብ ውስጥ የተፈጠረን አንድ አሳዛኝ አጋጣሚ ወደ መልካም ነገር በመቀየር የተቋቋመው የማቲዎስ ወንዱ የኢትዮጵያ ካንሰር ሶሳይቲ የሚሠራቸውን ሥራዎች በማሳደግ በአሁኑ ሰዓት ጤናማ አፍሪካ የሚል ትልቅ ፕሮጀክት ቀርጾ እውን ለማድረግ እየሠራ ይገኛል፡፡ ፕሮጀክቱ ተላላፊ ያልሆኑ ህመሞች የልህቀት ማዕከል ማቋቋም ሲሆን፣ ዋና ዓላማው ተላላፊ ስላልሆኑ በሽታዎች የግንዛቤ ማስጨበጫ፣ የልየታና የምርመራ ክፍል ለታካሚዎች እንክብካቤ በመስጠት እና ህሙማን ወደ ውጭ ሀገር ሄደው ለመታከም የሚያዩትን እንግልት ማስቀረት ነው፡፡

ማዕከሉ በውስጡ ከ45 በላይ የሥራ ክፍሎች (ዲፓርትመንቶች) ያሉት ዘመናዊ የምርመራና የሕክምና ማዕከላት፣ የምርምርና ስርጸት ማዕከል የህሙማንና ቤተሰቦቻቸው ማረፊያ፣ ጤናማ የአኗኗር ዘይቤን የሚያጎለብቱ የስፖርት ማዘውተሪያዎችና ካፍቴሪያዎች ለመገንባት በእቅድ ይዞ በመሥራት ላይ ይገኛል፡፡

እነዚህና መሰል ሀገር በቀል ተቋማት መስፋፋታቸው እንደሀገር ያሉብንን ችግሮች ከመቅረፍ እና በተለያዩ ዘርፎች የተሻለች ሀገር ለመገንባት ትልቅ አስተዋጽኦ ያለው በመሆኑ የሶሳይቲው ሥራ ይበል የሚያሰኝ ነው፡፡

# ወጣቶች

## ከጎዳና ኑሮ ወደ ስኬት ጉዞ

**ክብረአብ በላቸው**



ሕይወት ብዙ ፈተና እና ትግል የሚታለፍባት ተግባራዊ ትምህርት ቤት ናት። ብዙዎች ሲወድቁ አንዳንዶች ግን በድል ያልፋሉ። የሕይወት ፈተና ወደ መሬት ሲጥለን በወደቅንበት ቦታ ሆነን ማማረር ማጉረምረም ለመውደቁ ለመደናቀፉ ምክንያት የሆኑትን ሰዎች ሁኔታዎች እና ዕድለቢስነትን እየደጋገሙ ከማብራራት ይልቅ ወደላይ መመልከት ብቸኛው መፍትሔ ስለመሆኑ እሙን ነው።

የእዚች ዓለም ውጣ ውረድና የሕይወት ውስብስብ ፈተና አያልቅም። ሁሌም ቢሆን በሕይወት ውስጥ ክፍተት አለ። ሁልጊዜ ደስተኛ መሆን አይቻልም፤ አንዳንዴ መከፋት፣ ኀዘን ይኖራል፤ አንዳንዴም ማጣት ይከሰታል፣ ሁሉም ነገር አይሰጥም፤ ሁሉም ነገር ደግሞ አይታጣም። በሕይወት ውስጥ ሁሌም ክፍተት አለ፤ ግን ሕይወት ያመጣችውን ፈተና ተጋፍጦ ውጤታማ መሆን ለብርቱዎች የተሰጠ ፀጋ ነው።

የዛሬ የአዲስ ዘመን ወጣቶች አምድ እንግዳችን ወጣት ሽኩር አብደላ ይበላል። በመዲናችን አዲስ አበባ ከተማ ተወልዶ ያደገው ወጣቱ፤ ዛሬ እዚህ ስኬት ላይ ከመድረሱ በፊት እጅግ አስቸጋሪ የሕይወት ፈተና እንዳሳለፈ ይናገራል፡፡ ለረዥም ዓመታት በጎዳና ላይ በተለያዩ የከተማዋ አካባቢዎች እየተዘዋወረ ኑሮውን ያደረገው ሽኩር፤ ለመረማመጃነት እንጂ ለሰው ልጅ መኖሪያነት ባልተፈጠረ ቦታ ኑሮን መግፋት ከሚገመተው በላይ ስቃዩ ከባድ ስለመሆኑ ይናገራል።

ሕይወት ፊቷን አዙራበት ሳያስበው የጎዳና ተዳዳሪ የሆነው ሽኩር በክረምት ብርድ በበጋ በሐሩር ፀሐይ መሰቃየት የጎዳና ሕይወት የዕለት ተዕለት ዕጣ ፈንታ እንደሆነ ይናገራል፡፡ ይህ እንዳለ ሆኖ በጎዳና ለሚኖሩ ወጣቶች በማኅበረሰቡ ዘንድ ያለው አመለካከት ማለትም ዱርዬ፣ ሌባ ብቻ አድርጎ ማየቱ በከፍተኛ ደረጃ የሥነልቦና ጫና የሚያሳድር እንደሆነ ይገልፃል።

ወጣት ሽኩር እንደሚለው፤ የጎዳና ሕይወትን ለብዙ ዓመታት ሲያሳልፍ ፈታኝና ስቃይ የተሞላበት ሕይወት ስለመግፋቱ በምሬት ያስታውሳል። «እንደ ወንጀለኛ ስለምታይ ፖሊሶች ያባርሩኛል፤ ስታመም የምተኛበት ሕክምና የማገኝበት ሁኔታ አልነበረም፤ ከተገኘ የጉልበት ሥራ እሠራለሁ፣ ሥራ ሲጠፋ ደግሞ የሰው ፊት አያለሁ፤ የሆቴሎች ትራፊ ምግብ እበላለሁ፤ በቆሻሻ ገንዳ እየዞርኩ የሚሸጡ ዕቃዎች እየፈለግኩ እውላለሁ፡፡» የሚለው ወጣቱ የጎዳና ሕይወት እሱንም ሆነ ሌሎች ጓደኞቹን የሲጋራና የጫት ሱሰኛ አድርጓቸው እንደነበር ይናገራል።

ከእዚህ ሕይወት ለመውጣትና ሥራ በመሥራት እራሱን ለመለወጥ የወሰነው ወጣቱ፤ በቀላሉ ምን መሥራት እችላለሁ? ብሎ እራሱን ሲጠይቅ ወደ አዕምሮ የመጣው ብዙ ርቀት ሳይጓዝ በአካባቢው የሚገኘውን የደረቅ ቆሻሻ በመሰብሰብ መሸጥ ነበር። ይህንን ሥራ ከትንሽ ጀምሮ መሥራት ሲጀምር ውጤታማ እንደሚያደርገው በመገንዘቡ ሌሎች ጓደኞቹን በማስተባበር ሽኩርና ጓደኞቹ የተሰኘ የደረቅ ቆሻሻ ማስወገድ ላይ የተሰማራ ማኅበር መስርቶ ሥራውን እንደቀጠለ ይናገራል።

‹‹ወደዚህ ሥራ ስገባ ብዙዎች ውጤታማ አትሆንም ከማለት ባለፈ ይሳለቁብኝ ነበር›› የሚለው ሽኩር፤ ለራሱ ዛሬ ያለው ሁኔታ ጠንክሮ በመሥራት የሚለወጥ እንደሆነ በማመን ሰዎች ለሚሰጡት አሉታዊ አስተያየት ጆሮ ሳይሰጥ ሥራው ላይ ብቻ በማተኮር ስኬታማ መሆን እንደቻለ ይናገራል። በሀገሪቱ ሕዝብ አብዛኛውን የሰው ቁጥር የሚይዘው ሠርቶ ለመለወጥ አቅምና ጉልበቱ ያለው ወጣቱ ስለመሆኑ የሚናገረው ሽኩር፤ አብዛኛው ወጣት ግን ሥራ ሳይንቅ ሠርቶ እራሱን ለመለወጥ ያለው ፍላጐት የቀዘቀዘ ስለመሆኑ ይናገራል። ለእዚህ ማሳያው የሚለውንም ሲናገር፤ ብዙውን ጊዜ ከእርሱ ጋር ወጣቶች አብረውት እንዲሠሩ ለማድረግ ጥረት ቢያደርግም ሥራውን በመናቅና ስልቹ በመሆን እንደተለዩት ያስረዳል።

የደረቅ ቆሻሻ ማስወገድ ሥራው እነርሱ ከሚያገኙት ገቢ ባለፈ ከተማውን ውብና ፅዱ ለማድረግ ያለው አስተዋጽኦ ከፍተኛ እንደሆነ የሚናገረው ወጣት ሽኩር፤ ይህንን ሥራውን እርሱ በሚፈልገው ልክ መሥራት እንዳይችል ብዙ ተግዳሮት እያጋጠመው እንደሆነ ይገልፃል። አሁን ያሉበት በብዙ መልኩ ለሥራው አስቸጋሪ በመሆኑ ማለትም ለዚህ የሚሆን ቦታ አለማግኘታቸው ትልቅ ችግር ሆኖ ከፊታቸው እንደተጋረጠ ይናገራል።

በቀን ደረቅ ቆሻሻ እያቀረቡ የሚከፈላቸው ወጣቶችንና በወር ደሞዛቸውን የሚያገኙ ግለሰቦችን ሳይጨምር እስከ 20 የሚሆኑ ወጣቶችን በቋሚነት በስሩ የሚያስተዳድረው ወጣት ሽኩር፤ አሁን ላይ ደረቅ ቆሻሻን መልሶ አገልግሎት ላይ ለሚያውሉ ግለሰቦችና ድርጅቶች እንዲሁ ጥሬውን ከማቅረብ ፈጭቶ የተሻለ ገቢ የሚገኝበት ለማድረግ ለመሣሪያ ግዥ የሚሆን ፋይናንስ አለመኖር ሌላኛው የማኅበሩ ተግዳሮት እንደሆነ ይገልፃል፡፡ ይህ ችግራቸው ቢቀረፍ ከዚህ የበለጠ በመሥራት ለሌሎች የሥራ ዕድል መፍጠር እንደሚችሉ እራሳቸውም አሁን ካለው በተሻለ ሁኔታ ተጠቃሚ መሆን እንደሚችሉ ይናገራል።

«እዚህ ደረጃ ላይ የደረስነው ከምንም ተነስተን ነው፡፡» የሚለው ወጣት ሽኩር፤ የጉለሌ ክፍለ ከተማን ጨምሮ የወረዳ ሦስት ጉዳዩ የሚመለከታቸው አካላት ማኅበሩ ሌሎች ተሞክሮ ሊወስዱበት የሚችሉት ዓይነት ማኅበር በመሆኑ ክትትልና ድጋፍ በማድረግ ለውጤታማነታቸው አወንታዊ አስተዋጽኦ እንዳበረከቱ ተነግሯል።

ማኅበሩ አሁን ላይ 85 ሺህ ብር የሚሆን የቁጠባ ተቀማጭ ገንዘቡን ሳይጨምር ከ150 ሺህ ብር በላይ ካፒታል እንዳለው የተናገረው ወጣት ሽኩር፤ ከምንም ላይ ተነስተን ይህንን ሀብት ማፍራት መቻል እንደቀላል የሚታይ አይደለም፤ ነገር ግን ከዚህ በላይ ውጤታማ ለመሆንና አሁን ካለው የሠራተኛ ቁጥር በላይ በመቅጠር መስራት እንዲችሉ መንግሥት ከጎናቸው ሊቆም ይገባል ይላል። «ተነሳሽነት ከተላበስንና ውስጣችንን በማሳመን ያለመታከት ከሠራን ከባዶ ነገር በመነሳት ወደተሻለ ደረጃ መድረስ ይቻላል።» የሚለው ወጣቱ፤ እርሱ የመጣበት መንገድ ለዚህ ማሳያ ሆኖ ማቅረብ እንደሚቻል ይገልፃል።

እንደወጣቱ ገለፃ፤ በየዓመቱ ከፍተኛ ቁጥር ያላቸው ወጣቶች ከሀገሪቱ ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት በተለያየ የሙያ መስክ ይመረቃሉ፡፡ ነገር ግን የሥራ ዕድሉ አነስተኛ ነው። ሥራ ፈጠራ ደግሞ በትምህርት ብቻ የሚገኝ ነገር አይደለም፡፡ ተቀጣሪ ከመሆን ደግሞ የራስን ሥራ መስራት የተሻለ በመሆኑ ወጣቶች ሥራ ሳይንቁ መንቀሳቀስ አለባቸው።

ወጣት ሃዋ አብደላ ደግሞ ሌላኛዋ የእዚህ ማኅበር መሥራች አባል ናት። እርሷ እንደምትናገረው ወደዚህ ሥራ ከመምጣቷ በፊት እራሷንና ቤተሰቦቿን ለመደገፍ የተለያዩ ሥራዎችን ለመሥራት ሞክራለች፤ ቆሎ አዞሮ መሸጥ፣ የሰው ቤት በመዞር ልብስ ማጠብ፣ ጉሊት መሸጥ ሃዋ እራሷን ለመለወጥ ጥረት ያደረገችባቸው ሥራዎች ናቸው፡፡ ከዚህ ባለፈ ስደትን አማራጭ በማድረግ በውጭ ሀገር ቆይታ አድርጋ እንደመጣች ትናገራለች።

ብዙ ነገር ለመሥራት ብትሞክርም ‹‹ውጤታማ መሆን የቻልኩት በዚህ ሥራ ነው›› የምትለው ሃዋ፤ ጫናው ቢበረታም ከሌላ ሥራ ከሚገኘው ገቢ ይልቅ፤ ይህ ሥራ ካለው ፋይዳ አንፃርም ከመንግሥት አካላት ጀምሮ የማበረታታት እንጂ እንቅፋት የሚኮንበት ሁኔታ ባለመኖሩ አዋጭ እንደሆነ ትገልፃለች።

በዓይን ሲታይ የሚሠራው ሥራ ቆሻሻ ሊመስል ይችላል፡፡ ቀርቦ ላየው ሰው ግን ገንዘብ ነው የምትለው ሃዋ፤ ሁሉም ነገር ወደ ገንዘብ የሚቀየር እንደሆነ ትናገራለች። በሀገር ውስጥ የተለያዩ ሥራዎችን ከመሥራት ጀምሮ ባሕር ተሻግራ የሰው ሀገር በመጓዝ ለሦስት ዓመታት ኑሮን ለማሸነፍ ጥረት ያደረገችው ሃዋ፤ «በዚህ ሁሉ ደስተኛ አልነበርኩም አሁን ግን በዚህ የሥራ ቦታ ስውል ቤቴ ሁሌ ትዝ አይለኝም፤ ከተማውን ፅዱ በማድረግ ገቢ እያገኘን መሆኑ ደስተኛ አድርጎኛል»ትላለች።

‹‹ሥራን ባለመፀየፍ ከሠራን ፈተና የሚሆን ነገር ቢኖርም እርሱን አሸንፎ በመውጣት ካለሙበት መድረስ እንደሚቻል አምናለሁ» የምትለው ሃዋ፤ በፍቅር በጋራ መሥራት ደግሞ ይበልጥ ለውጤታማነት አጋዥ መሆኑን ታስረዳለች። ማኅበሩም በጥቂት ጊዜ ትርፋማ እንዲሆን በአባላቱ መካከል ቤተሰባዊ ግንኙነት መኖር በእጅጉ እንደጠቀማቸው ታስረዳለች።

ሃዋ እንደምትናገረው፤ በአካባቢዋ ለምታውቃቸው ጓደኞች በማኅበራቸው ስር ከሚሠሩ ሥራዎች በአንፃራዊነት ቀላል የሆነውን የፕላስቲክ ኩዳን በመፍታት አንድ ኪሎ የሚሆን በመሰብሰብ ገንዘብ እንዲያገኙ ለማድረግ ጥረት ብታደርግም ይህንን እንኳ ለማድረግ ብዙዎቹ ቆሻሻ ነው ብለው ስለሚያስቡ እንደሚፀያፉት ትናገራለች።

ከዚህ በፊት እርሷም ሥራውን እሩቅ ሆና ስታየው የነበራት አመለካከት የንቀት እንደነበር የምትናገረው ወጣት ሃዋ፤ የቆሻሻ ክምችት ብቻ እንደሚመስላት፣ ቀርባ ስትመለከተው ግን ገንዘብ የሚገኝበት ሆኖ እንዳገኘችው፤ ይህም ሥራውን እንድትወደው ምክንያት እንደሆናት ተናግራ፤ ስለዚህ ማንኛውም ወጣት በእሩቁ ውጤታማ አያደርገኝም ብሎ ከመበየን ቀርቦ አይቶ መወሰን እንዳለበት ትመክራለች።

አቶ ሀብታሙ አያሌው በጉለሌ ክፍለ ከተማ ወረዳ ሦስት የፅዳት አስተዳደርና መልሶ መጠቀም ባለሙያ ናቸው፡፡ እርሳቸው እንደሚናገሩት፤ የመሥሪያ ቤቱ ኃላፊነት ወረቀት፣ ካርቶን፣ ሌሎች የፕላስቲክ ቆሻሻዎችን መልሶ ጥቅም ላይ እንዲውሉ ማድረግ ነው። ይህንን ሥራ ለማከናወን ሥራ አጥ ወጣቶችን በማደራጀት ወደ ሥራ ማስማራት ነው።

ባለሙያው እንደሚሉት፤ ወጣቶችን አደራጅተው ይህንን ሥራ እንዲሠሩ ለማድረግ በተለያየ ጊዜ እንደ ወረዳ ባደረጉት ጥረት ሁለት ሦስት ማኅበራት አንደኛ ሥራውን ባለማወቅ፣ ሁለተኛ ደግሞ ስልቹ በመሆንና ለሥራው ባላቸው ዝቅተኛ አመለካከት ምክንያት ሥራውን አቁመው የተበደሩትን ገንዘብ እንኳ መክፈል ሳይችሉ ተበትነዋል፡፡ በዚህ ምክንያት ሽኩርና ጓደኞቹ የእንደራጅ ጥያቄ ሲቀርብ በሙሉ እምነት ወደ ሥራው እንዲገቡ ለማድረግና መለወጥ እንደሚችሉ ለወራት ስለሥራው የግንዛቤ ማስጨበጥ ሥራ እንደተሠራ ይናገራሉ።

የተለያዩ ተቋማትን በር በማንኳኳት ለዚህ ማኅበር ድጋፍ እንዲያደርጉ ጥረት ማድረጋቸውን የሚገልፁት አቶ ሀብታሙ፤ ከክፍለ ከተማ፣ ከማኅበራት ማደራጃ ኤጀንሲ፣ ከወረዳ ጨምሮ ድጋፍ አድርገው አሁን የሚሠሩበትን ኮንቴነር እንዲያገኙ ተሠርቷል ይላሉ። አሁን ላይ ግን የሚሠሩት ሥራ ከመስፋቱ የተነሳ ያሉበት ቦታ ለሥራው አመቺ ባለመሆኑ ከዚህ የተሻለ ቦታ እንዲሰጣቸው እየጠየቁ መሆኑን ተናግረዋል። ለእዚህ ችግራቸው መፍትሔ ለመስጠት ከተማ አስተዳደሩ ወይም ክፍለ ከተማው ቢሠራ መልካም ነው ይላሉ።

አሁን በአጠቃላይ በጉለሌ ክፍለ ከተማ ስር ያሉ በተናጠል የደረቅ ቆሻሻ ማስወገድ ላይ የተሰማሩ ማኅበራት ለሽኩርና ጓደኞቹ ማኅበር እንዲያስረክቡ ለማድረግ እየተሠራ ነው የሚሉት ባለሙያው፤ ይህም ሁሉንም ተጠቃሚ የሚያደርግ በመሆኑ በፍጥነት ተግባራዊ ለማድረግ እንቅስቃሴ ስለመጀመሩ ይገልፃሉ።

እንደ አቶ ሀብታሙ ገለፃ፤ በኢትዮጵያ በዓመት እስከ ሁለት ሚሊዮን የሚጠጉ ወጣቶች ወደ ሥራ ዓለም ይቀላቀላሉ ወይም ሥራ ፈለጊ ይሆናሉ። ለእዚህ ብዙ ቁጥር ላለው ዜጋ በመንግሥት ወይም በግል ተቋማት እና ድርጅቶች የሥራ ዕድል መፍጠር ባለመቻሉ ደግሞ አብዛኛዎቹ ለሥራ አጥነት ይዳረጋሉ። ይህንን ችግር ለመፍታት ደግሞ ሥራ ጠባቂ ከመሆን ይልቅ ሥራ ፈጣሪ ሆኖ መገኘት የሚጠበቅ ሆኗል ይላሉ።

በሀገሪቱ በርካታ ወጣቶች የሥራ ፈጠራ ባለሙያዎች ቢሆኑም የፈጠራ ሃሳባቸውን ወደ ተግባር ለማዋል የመሥሪያ ቦታ እጥረት፣ የብድር አቅርቦት አለመመቻቸት፣ የገበያ ትስስር አለመኖር እና የክህሎት ክፍተቶች እንቅፋት ስለሆነባቸው፤ ይህንን ችግር ለመፍታት ሁሉም ባለድርሻ አካላት ጥረት ማድረግ እንዳለባቸው ተናግረዋል።

# የምድር በረከት

## የ«ሶዳ አሽን» ፍላጎት -በሀገር ውስጥ ምርት

**ወርቅነሽ ደምሰው**



**በአብያታና በሻላ ሐይቅ ከ380 ሚሊዮን ቶን በላይ የሚገመት የሶዳ አሽ ማዕድን ክምችት ይገኛል፤**

በኢትዮጵያ ከሚገኙና እንዲለሙ ከተደረጉ በርካታ ማዕድናት መካከል ሶዳ አሽ የተሰኘው ማዕድን አንዱ ነው፡፡ በሀገሪቱ የተለያዩ አካባቢዎች ከፍተኛ መጠን ያለው የሶዳ አሽ ማዕድን ክምችት መኖሩን መረጃዎች ይጠቁማሉ። ማዕድኑ በብዛት ይገኝባቸዋል ተብለው በጥናት ከተለዩት ቦታዎች መካከል መንትዮቹ በመባል የሚታወቁት የአብያታ እና የሻላ ሐይቆች በዋናነት ይጠቀሳሉ፡፡ በአፋር ክልል ዳሎል አካባቢም እንዲሁ ማዕድኑ እንደሚገኝ መረጃዎች ያመላክታሉ፡፡

ሶዳ አሽ ለኢንዱስትሪዎች ግብዓትነት ይውላል፤ ለሳሙና፣ ጨርቃጨርቅ፣ ቆዳ፣ ብርጭቆ እና ወረቀት ፋብሪካዎች በእጅጉ ያስፈልጋል፡፡ ይህ ማዕድን በተፈጥሮ በአፈር መልኩ ተቀልሎ እንዲሁም በሐይቅ ውስጥ ይገኛል።

አሁን ላይ እንደ ሀገር እየለማ ያለው ሶዳ አሽ ማዕድን ግን በሐይቅ ውስጥ የሚገኘው ነው። ማዕድኑ እንዳለበት የተለየው ውሃ በተለያዩ ኩሬዎች እንዲጠራቀም ይደረጋል፤ ውሃው በፀሐይ ብርሃን እንዲተን የማድረግ አሠራርን በመከተል ሶዳ አሹን የመለየት ሥራ ይከናወናል።

መረጃዎች እንደሚጠቁሙት፤ በአብያታና በሻላ ሐይቅ ከ380 ሚሊዮን ቶን በላይ የሚገመት የሶዳ አሽ ማዕድን ክምችት ይገኛል። በእነዚህ ሐይቆች ላይ ማዕድኑን ለማምረት የሚያስችለውን ፈቃድ ወስዶ እየሠራ ያለው የአብያታ-ሻላ ሶዳ አሽ አክሲዮን ማኅበር ነው። ማኅበሩ በሜድሮክ ኩባንያና በመንግሥት ሼር የተቋቋመ ሲሆን፤ በኦሮሚያ ክልል ምሥራቅ ሸዋ ዞን አዳሚ ቱሉ ጂዶ ኮምቦልቻ ወረዳ ፋብሪካ በመገንባት የሶዳ አሽ ማዕድን የማምረት ሥራውን እያካሄደ ነው፡፡

የአብያታ ሻላ ሶዳ አሽ አክሲዮን ማኅበር የንግድ ሥራ ዋና ክፍል ኃላፊ አቶ ገመቹ ነገራ እንዳስታወቁት፤ ማኅበሩ የሶዳ አሽ ማዕድን ለማምረት የሚያስችለውን ፋብሪካ በመገንባት ወደ ምርት ከገባ ቆይቷል፡፡ አክሲዮን ማኅበሩ በሶዳ አሽ ማዕድን ሥራ ላይ እንዲሰማራ ካስቻሉት ዋንኛ ምክንያቶች አንዱ በአብያታና ሻላ ሐይቆች ያለው ሰፊና እምቅ የሶዳ አሽ የማዕድን ክምችትና ምርቱ የሚፈልጉ በርካታ ኢንዱስትሪዎች በመኖራቸውም ነው፡፡

አቶ ገመቹ ቀደም ብሎ የተደረገ ጥናትን ዋቢ በማድረግም ስለማዕድኑ ሲያብራሩም እንደ ሀገር በዚህ ማዕድን ልማት ሰፊ ሥራ መሥራት እንደሚቻልና የሚመረተው የሶዳ አሽ ማዕድንም ለሀገር ውስጥ የኢንዱስትሪዎች ግብዓት ከማዋል ባሻገር ለውጭ ገበያ ማቅረብ የሚቻልበት ዕድል መኖሩን አብራርተዋል፡፡

እንደ አቶ ገመቹ ገለጻ፤ ‹ሶዳ አሽ› Soda ash ($Na_2CO_3$) ሲባል ማዕድኑ ያለበትን ውሃ ከሐይቅ ስቦ በማውጣት በኩሬ እንዲታቆር ከተደረገ በኋላ በፀሐይ ኃይል ውሃው እንዲተን ሲደረግ የሚቀረው ቶሮና ይባላል፡፡ ቶሮና በመባል የሚታወቀው ሶዳ አሽ የተሰኘው ማዕድን በውስጡ ባይካርቦኔት፣ ሶዴየም ባይካርቦኔት፣ የተሰኙ ማዕድናትን ይይዛል፡፡ ይህም በላቦራቶሪ እንዲታይ ተደርጎ ትክክለኛው የሶዳ አሽ ማዕድን እንዲመረት ይደረጋል፡፡

ሶዳ አሹ በሸርክት ወይም በደቀቀ መልኩ ተፈጭቶ ለገበያ ሊቀርብ እንደሚችል ጠቅሰውም፤ ለሳሙና እና ለዲተርጀንት፣ ለጨርቃ ጨርቅ፣ ለቆዳ፣ ለብርጭቆና ለወረቀት ፋብሪካዎች በጥሬ በግብዓትነት የሚውል መሆኑን ይናገራሉ፡፡ በተለይ የሳሙና እና ለዲተርጀንት ፋብሪካዎች ትልቁ ግብዓት መሆኑን አመላክተዋል፡፡

በዚህ የማዕድን አወጣጥ ሂደት ምንም ዓይነት ኬሚካል ሥራ ላይ እንደማይውል ጠቅሰው፣ አካባቢውን የመበከልም ሆነ ሌላ ምንም ዓይነት የጎንዮሽ ጉዳት እንደማያደርስም ይገልጻሉ፡፡

የሶዳ አሽ ማዕድን ለማምረት የታቆረው ውሃ በፀሐይ ኃይል አማካይነት እንዲተን ይደረጋል። ማዕድኑ ጨዋማ መሆኑን ጠቅሰው፤ የሶዳ-አሹ ከጨው በላብራቶሪ ይለያል፤ በመቀጠልም ለኢንዱስትሪዎች ግብዓትነት እንዲውል በሚፈለገው መጠን እንዲዘጋጅ ይደረጋል። ኢንዱስትሪዎች የሶዳ-አሽ ምርት ሲፈልጉ በሚያቀርቡት ዝርዝር የመጠን መገለጫ የሚፈልጉት ያህል መጠን በላቦራቶሪ ተለይቶና ተዘጋጅቶ እንደሚቀርብላቸው ነው ያስረዱት፡፡

ፋብሪካው እስካሁን ሶዳ አሽ የማምረት ሥራውን በአብያታ ሐይቅ ላይ እየሠራ መሆኑን ይገልፃሉ፡፡ በአሁኑ ወቅት ከ200 በላይ ለሚሆኑ ቋሚ ሠራተኞች እና በርካታ ጊዜያዊ ሠራተኞችም የሥራ ዕድል መፍጠሩን አስታውቀዋል፡፡

እንደ አቶ ገመቹ ገለፃ፤ ሶዳ አሽ የማምረቱ ሥራ ዝናብ ካልበዛ በስተቀር በስፋት ይካሄዳል፤ ከዝናብ መብዛት ጋር በተያያዘ ግን የሚስተጓጎልበት ሁኔታ ያጋጥማል። ለአብነትም ዘንድሮ የክረምት ወቅቱ በመረዘሙ ምክንያት ማዕድን ያለውን ውሃ ከሐይቅ በማውጣት በኩሬ እንዲታቀፍ ቢደረግም፣ እስካሁን ውሃው በፀሐይ ኃይል ሊተን ባለመቻሉ የሚፈለውን ያህል ማዕድን ለማግኘት አልተቻለም፡፡ በማዕድን ማውጣቱ እንዲካተት የሚያስፈልገው ቶሮና የተባለው ተፈላጊ ነገር ሳይሠራና የፀሐይ ኃይል ሳያገኝ ቆይቷል፡፡

በሌላ በኩል ደግሞ ውሃ በሚሸሽት ወቅትም እንዲሁ ምርቱ እንደማይመረት ተናግረዋል። ከዚህ ቀደም ውሃ የሸሸበት ሁኔታ ተከሰቶ እንደነበርም አቶ ገመቹ አስታውሰዋል፡፡

እነዚህ ችግሮች ድርጅቱን ለተለያዩ ተደራራቢ ወጪዎች እንደሚዳርጉትም ያመለክታሉ፡፡ የክረምቱ ወራት በሚያጥርበት ጊዜ ግን የተሻለ ምርት ማምረት እንደሚቻል ገልጸው፤ በተለይ በባለፈው አመት አስደሳች ውጤት መገኘቱን ጠቅሰዋል፡፡

ሶዳ አሽ የማምረቱ ሂደት በተፈጥሮ ላይ መሠረት እንደሚያደርግ ጠቅሰው፣ በመጀመሪያው ስድስት ወራት የተፈለገውን ያህል ምርት ባይመረትም፣ በቀጣይ ስድስት ወራት ያለው የአየር ንብረት እየተስተካከለ ሲሄድ ሶዳ አሽ ለማምረት ምቹ ሁኔታ ይፈጠራል፤ ያን ጊዜ ፋብሪካው ወደ ማምረት ሥራው በስፋት እንደሚገባ ነው ያስገነዘቡት፡፡

በዚህ የማዕድን ልማት ሥራ ያጋጠሙ ብዙ ተግዳሮቶች እንደሌሉ የሚናገሩት አቶ ገመቹ፤ ለልማት ዋንኛ የሆነው እንደ ሀገር እየታየ ያለው የሰላምና የመረጋጋት ችግር አሉታዊ ተጽዕኖ እየፈጠረ እንደሆነ ይገልጻሉ፡፡

‹‹በሀገራችን ያለው የሶዳ አሽ ማዕድን ከፍተኛ ክምችት በዘርፉ ለመስማራት መልካም አጋጣሚን ፈጥሯል›› ያሉት አቶ ገመቹ፤ በማዕድን ሥራው ልምድ ያላቸው ሰዎችን ማግኘት መቻሉ በቀላሉ ወደ ሥራው መግባት ማስቻሉንም ያስረዳሉ፡፡

እንደ አቶ ገመቹ ገለፃ፤ የሶዳ አሽ ማዕድን አስፈላጊና ለተለያዩ ምርቶች በጥሬ ግብዓት ያገለግላል፡፡ ፋብሪካው ደግሞ ሶዳ አሽን በማምረት ለሀገሪቱ ኢንዱስትሪዎች ያቀርባል። ይህም ማዕድኑን በሀገር ውስጥ ለማምረት የሚያስችል አቅም ከመፈጠር ባሻገር ምርቱን ከውጭ ለማምጣት ይውል የነበረውን ከፍተኛ የውጭ ምንዛሬ ያስቀራል፡፡ ምርቱን ለውጭ ገበያ በመላክ የውጭ ምንዛሪን ማግኘትም የሚያስችል አቅምን ይፈጥራል፡፡

‹‹የሶዳ አሽ ከተመረተ በኋላ ፈላጊዎቹ ብዙ ስለሆኑ በቀላሉ ገበያ ማግኘት ችለናል›› ያሉት አቶ ገመቹ፤ ከአምራቹ የሚጠበቀው የጥራት ደረጃ ከፍ በማድረግ ፋብሪካዎች በሚፈልጉት መጠን ማምረት መሆኑን ይገልጻሉ፡፡

በአፍሪካ ቀንድ እንደኬንያ ያሉ ሀገራት ሶዳ አሽን በማምረት የሚታወቁ ሲሆን፤ ቻይናም በእዚህ ምርት ትጠቀሳለች፡፡ ቀደም ሲል ሶዳ አሽ በጥሬ ግብዓትነት የሚጠቀሙ ፋብሪካዎች ይህን ግብዓት ከቻይናና ከኬንያ እያስመጡ ይጠቀሙ እንደነበር አቶ ገመቹ አስታውሰው፤ የአብያታ-ሻላ የሶዳ አሽ ፋብሪካ ከተቋቋመ ጊዜ ወዲህ አብዛኞቹ ፋብሪካዎች የሚፈለጉትን የሶዳ አሽ መጠን በዝርዝር አቅርበው ምርቱን የሚወሰዱበት አሠራር ተዘርግቶ እየተሠራ እንደሆነ ያብራራሉ፡፡

እንደ አቶ ገመቹ ማብራሪያ፤ የሶዳ አሽ ማዕድን ምርት እጅግ ተፈላጊና የበርካታ ፋብሪካ ግብዓት ሲሆን፣ ፋብሪካውም ይህንን ምርት የሚያመርተው ጥራቱን በጠበቀ መልኩ ነው፡፡ ጥራቱን የጠበቀ ከውጭ የሚመጣውን የሚስተካከል ምርት ያመርታል። ሀገር ውስጥ ላሉ ፋብሪካዎች በሚፈለጉት መጠንና ጥራት ምርቱን ለማቅረብ በላቦራቶሪ ተፈትሾ የሚወጣ ስለሆነ እስካሁን በዚህ ዙሪያ ፋብሪካው ችግር አልገጠመውም፡፡ በቀጣይ የተሻለ ጥራት ያለው ምርት በማምረት በእቅድ ተይዞ እየተሠራ ሲሆን፤ ጥራቱ የሚለካበትን የተሻለ የቴክኖሎጂ ደረጃ ያላቸው የላቦራቶሪ መሣሪያዎች ለማስገባት ታቅዷል፡፡

‹‹ድርጅቱበማዕድንልማትላይከመሰማራት ባሻገር በአካባቢው ያለውን ኅብረተሰብ የልማቱ ተሳታፊ እንዲሆን በማድረግ ረገድም እየሠራ ነው›› ይላሉ። በዚህም ማኅበራዊ ኃላፊነቱን እየተወጣ እንደሆነም ይናገራሉ፡፡ የማዕድን ልማቱ በሚሠራበት ቦታ ላይ ያለው ኅብረተሰብ የሚፈለገውን የጤና፣ የውሃ እና የመሳሰሉት መሠረታዊ የልማት ጥያቄዎች ሲያቀርብ ድርጅቱ በሚችለው አቅም ልማቱን በማገዝ ከኅብረተሰቡ ጋር በጥምረት እየሠራ መሆኑንም ነው የጠቆሙት፡፡

‹‹በአሁኑ ወቅት የሶዳ አሽ ማዕድን በተለያዩ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ እንደሚገኝ የሚጠቁሙ አመላካቾች አሉ›› ያሉት አቶ ገመቹ፤ ለአብነት በአፋር ክልል ውሃ ማቆርና ማትነን ሳይጠበቅበት ራሱ በተፈጥሮ ቶሮና በመባል የሚታወቀው ተዘጋጅቶ በአፈር መልክ ተቀምጦ እንዳለ መረጃዎች አጣቅሰው ይናገራሉ፡፡ ይህም በሌሎች አካባቢዎችም ጥናት ቢደረግ ማዕድኑ ሊገኝ እንደሚችል እንደሚያመላክት ይገልፃሉ፡፡

ሀገሪቱ ብዙ የማዕድን ሀብት እንዳላት ቢነገርም እየተሠራባቸው ያሉት ወርቅና በመሳሰሉት ላይ ብቻ እንደሆነ ይጠቅሳሉ። ሀገሪቱ ያላት እምቅ የማዕድን ሀብት ጥቅም ላይ በማዋል ረገድ ባለሀብቶች፣ ዲያስፖራዎች ከመንግሥት ጋር ተቀናጅተው ቢሠሩ ተጠቃሚ እንደሚሆኑ ይናገራሉ፡፡ ‹‹በተሰጠን የማዕድን ሀብት ላይ ብንሰራና ብንጠቀመበት ጥሩ ለውጦችንና ውጤቶችን ማምጣት እንችላለን›› ሲሉም ያስገነዝባሉ፡፡

የማዕድን ሀብቱ ትልቅ ኢንቨስትመንት ቢሠራ ከውጭ የሚገቡ ምርቶች በሀገር ውስጥ ከመተካት ባሻገር ወደ ውጭ በመላክ ከፍተኛ የውጭ ምንዛሪ ማስገኘት የሚችል ዘርፍ ነው ያሉት ገመቹ፤ የበለጠ ትኩረት ተሰጥቶት ሊሠራበት እንደሚገባም ይጠቁማሉ፡፡

በቀጣይም ሁለተኛውን የሻለ ሐይቅ ፕሮጀክት ለመጀመር ጥናቶች እየተካሄዱ መሆናቸውን ጠቁመዋል፡፡ በተለይ ሻለ ሐይቅ ሰፊ ማዕድን ያለበት መሆኑን ጠቅሰው፣ ሰፊ ሥራዎች ለመሥራት ያስችላል ብለዋል። ከሶዳ አሽ ምርት ለሀገር ውስጥ ግብዓትነት ከመጠቀም ባሻገር ለውጭ ገበያ የመላክ እቅድ ተያዞ እየተሠራ ነው፡፡ ይህም ሥራ ሲጀምር ለብዙዎች የሥራ ዕድል እንደሚፈጥር ይጠበቃል ሲሉ ነው አቶ ገመቹ ያስገነዘቡት፡፡

ከኃላፊው ማብራሪያ መረዳት እንደተቻለው፤ ሶዳ አሽ በውጭ ምንዛሬ ከውጭ ሲገባ የቆየ ሲሆን፣ ፋብሪካው ይህን ከውጭ ሀገር የሚመጣውን የሶዳ አሽ ምርት በሀገር ውስጥ ምርት በመተካት የውጭ ምንዛሬ ወጪን ማዳን ችሏል፡፡ ከዚህ አልፎም ምርቱን ለውጭ ገበያ ማቅረብ የሚቻልበት ሁኔታ እንዳለ ተመላክቷል።

ይህ ፋብሪካው እያከናወነ ያለው ተግባር መንግሥት ተኪ ምርቶችን በሀገር ውስጥ በማምረት የውጭ ምንዛሬ ወጪን ለማዳን ለያዘው አቅጣጫ ትልቅ አቅም በመሆን ያገለግላል፡፡ ፋብሪካው ይህን ሥራውን በሻላ ሐይቅ በማስፋፋት ሀገርን መደገፉን አጠናክሮ መቀጠል ይኖርበታል፡፡

መዝናኛ

# የብዕር ጠብታ

## ህልም ፈቺው

በትረ ሙሴ (መልከ ኢትዮጵ)

አባባ መርዕድ መንደሩ ውስጥ የታወቁ ህልም ፈቺ ናቸው፡፡ እሳቸው ጋ ሄዶ ህልሙን ያላስፈታ አንድም ሰው አይገኝም፡፡ ስለእሳቸው የህልም ጥበብ ወሬ ነጋሪ ሆነው ለመንደሩ ሰው ወሬ የሚነዙ በርካታ ወሬኞች አሉ፡፡ ወሬኞች እሳቸውን በማስተዋወቃቸው ብቻ ለሳምንት ህልማቸው በነፃ ይፈታላቸዋል። የዚህ ዕድል ተጠቃሚ ከሆኑት ውስጥ እትዬ ትብለጥ አንዷ ናቸው፡ ፡ እትዬ ትብለጥ ከመንደር መንደር፣ ከከተማ ከተማ እየዞሩ ስለ አባባ መርዕድ የሚመሰክሩ ሴት ናቸው፡፡ «የተናገሩት መሬት ጠብ አይልም፣ ቢበዛ በሰልስቱ አልያም በነጋታው ትንቢታቸው ይፈጸማል፣ በዚህ ጥበባቸው የመንደሩ ሰው ‘ሁለተኛው እግዜር’ የሚል ስም ሰቷቸዋል» እያሉ በበሬ ወለደ የሚያወሩና የሚያስወሩ ሴት ናቸው፡፡

አባባ መርዕድ እንደ ዕድሜአቸው መካሪና አስታራቂ ሳይሆኑ ዋሽቶ በማጣላት ምንዳ የሚፈልጉ ናቸው፡፡ አባትነታቸውን ለበጎ ሳይሆን ለነውር የሚጠቀሙ በበሬ ወለድ የቆሙ አዛውንትም ናቸው፡፡ በሽምግልናቸው ውስጥ ዘልቆ የገባ አንድ ነውር ቢኖር የገንዘብ ፍቅር ነው፡፡ ከእርጅናቸው ጋር የተስማማው ሽበቶ ጸጉራቸው እብለታቸውን ደብቆ ከእግዜር ጋር የቀረበ ወዳጅነት ያላቸው ጻድቅ ሰው አስመስሏቸዋል፡፡ በዕድሜ ነቁጥ የተዋጀ አንቱታነታቸው በእውነት እንጂ በግፍ የሚሞግተው አንድም ሰው የለም። ግን አባባ መርዕድ እንዲህ አይደሉም . . . በሽምግልናቸው ውስጥ እውነትና ፍትህ የለም፡፡

ለገንዘብ ካላቸው ስር የሰደደ ፍቅር ህልም ሊያስፈታ ወደ ታዛቸው የመጣን ደንበኛ የሚጠይቁት የመጀመሪያ ጥያቄ «ምን ያህል ህልም ይዘህ መጣህ? ከትናንት ማታ ጀምረን አንድ ህልም ብቻ ይዞ የመጣን ደንበኛ ማስተናገድ አቁመናል» የሚል ነው፡፡ ይሄው የነዋይ ፍቅራቸው ራሳቸው ላይ ወጥቶ ከሰሞኑ ደግሞ በአዲስ ውሸት ተከስተዋል፡፡ ወደ እሳቸው የመጣን ህልመኛ ሁሉ «ምን ላይ ሆነህ ነው ያለምከው? አልጋ ላይ ነው መደብ ላይ?» ሲሉ መጠየቅ ጀምረዋል፡፡ በሰሞነኛው በእሳቸው ሕግ መሠረት አልጋ ላይ ሆኖ ያለመና መደብ ላይ ተኝቶ ያለመ እኩል አይዳኝም፡፡ አባባ መርዕድ ፍትህን አያውቁም . . . የእውነት ስፍራው የት ጋ እንደሆነ አልደረሱበትም፡፡ ከትናንት እስከ ዛሬ ገንዘብ ለማግኘት ሲሉ ያልሠሩት የሸር ሥራ የለም፡፡ ሲያልቅ አያምር እንዲሉ ዛሬም በመቁረቢያ ዕድሜአቸው በእርጅና ህልም ፈቺ ሆነው ብቅ አሉ . . .፡፡ «እንዴት ብዬ ሌሎችን ላግዝ?» ሳይሆን «እንዴት ብዬ በሌሎች ላትርፍ?» የሚል የሽምግልና ቆፈን የተጠናወታቸው የዕድሜ ነውረኛ ናቸው፡፡፡

አዳፋ ብሉኳቸውን ወደ ትከሻቸው እያጣፉ . . . ከፀሐይ መውጫ ትይዩ በጎለቱት ባለመደገፊያ ወንበራቸው ላይ ተቀምጠው ህልመኛ ይጠብቃሉ።

ህልመኛ ይመጣል . . .

«ህልም እንዴት ነው?» ይጠይቃሉ፡፡

«ምንም አይል ጥሩ ነው» ህልመኛ ይመልሳል።

«ምን ላይ ሆነህ ነው ያለምከው? ማለቴ አልጋ ላይ ነው ወይስ አሊቤርጎ ሴት ጉያ ውስጥ? ህልም ሲፈታ ይሄ ሁሉ መታወቅ ይኖርታል . . . ያለዛ ጥበቤም እሺ አይለኝ፡፡» ሲሉ የባጥ የቆጡን ለፈለፉ፡፡

«ሶፋ ላይ ሆኜ ነው» ህልመኛ መለሰ፡፡

«እንደዛ ከሆነ በምኞት ያለምከበትን አምስት ብር ያስጨምርሀል፡፡ ከኑሮ ውድነቱ ጋር በተያያዘ በአንዳንድ ነገሮች ላይ የዋጋ ጭማሪ አድርገናል፡፡ ፍንጭት ጥርሳቸውን እያሳዩት። ይቺ ንግግራቸው የተለመደች ናት . . . መደብ ላይ ሆኜ ነው ያለምኩት ቢባሉ እንኳን ያለምኾት እየተወራጨህ ያለምከው ህልም ውስጠ ግንዱን ለማግኘት አስቸጋሪ ስለሚሆን ያስጨምርሀል ይላሉ እንጂ፣ ካለምኞት የታለመ ስለሆነ ቀንሼልሀለሁ አይሉም፡፡ ሰማይ ዝቅ ምድር ከፍ ቢል ዋሽተው ያተርፋሉ እንጂ ታምነው አያጎድሉም፡፡

«ህልሜን ይፍቱልኝ እንጂ ለብሩ ችግር የለውም» ህልመኛው መለሰላቸው፡፡

አባባ መርዕድ እጅጉን አዘኑ . . . አስርና ሃያ ብር ትጨምራለህ ባለማለታቸው ተቆጩ፡፡

......

እማማ ያሸርግዱ ከእትዬ ትብለጥ ቀጥለው የአባባ መርዕድ የህልም ደንበኛ ናቸው፡፡ አንዱም አይስመርላቸው እንጂ ከትናንት እስከዛሬ ያላስፈቱት አንድም ህልም የለም፡፡ ጠዋት . . . በጣም ጠዋት ለማኝ ሳይጸዳዳ በውርጩ የአባባ መርዕድን ቤት ከሚያንኳኩ እንስቶች አንዷ እማማ ያሸርግዱ ናቸው፡፡

«እንደው ዛሬ ምን ሊያሳየኝ ይሆን እንዲችው ሲያሰቃየኝ ነው ያደረው» ይላሉ እማማ ያሸርግዱ አባባ መርዕድ ፊት ላይ ተነጥፈው፡፡ እግዜራቸው ይመስል ከጉድ እንዲያወጧቸው በመማጸን ዓይነት፡፡

እማማ ያሸርግዱ ቀን ተኝተው ያለሙትን ሁሉ ያስፈታሉ ይባላል፡፡ ለህልም ካላቸው ፍቅር የተነሳ በቀን ሃያ አራት ሰዓት ነው የሚተኙት እየተባሉም ይታማሉ፡፡ አባባ መርዕድ ቤት ሲመላለሱ እንዲችው ነግቶ ይመሻል፡፡

የእማማ ያሸርግዱን እግር ተከትለው ሊነጋጋ ሲከጃጅለው እትዬ ትብለጥ ይመጣሉ። ሦስተኛው ሰው ሆነው የአባባ መርዕድን ደጅ በማለዳ ከሚረግጡት ውስጥ አቶ መንገሻ አንዱ ናቸው፡፡ አባባ መርዕድ ይሄን ሥራ የጀመሩት በእኚህ ሦስት ሰዎች ህልም ላይ ተለማምደው ነው ይባላል፡፡

እማማ ያሸርግዱ አባባ መርዕድ ቤት በመመላለስ ያተረፉት ነገር ቢኖር የጫማቸውን ሶል መጨረስ ብቻ ነው፡፡ በሁለት አመት ውስጥ ሃያ ስምንት ጥንድ ጫማዎችን ጨርሰዋል፡፡ ቀንና ሌሊት እያለሙ፣ ቀንና ማታ እያስፈቱ . . . ብርድ ሳይሉ ውርጭ ከአባባ መርዕድ ደጅ እየቆሙ «በሀብትና በሲሳይ ትሽቆጠቆጫለሽ»፣ «ይሄ ነው የማይባል ተድላ ቤትሽ ይገባል» የሚለው ትንቢታቸው ግን የምጻት ቀንን ያክል ርቋቸው በተስፋ ስብራት ውስጥ ወድቀዋል፡፡ በተስፋ ስብራታቸው ውስጥ ትናንትን ሲዳብሱት አጡት . . . ዛሬን ሲፈልጉት የለም፡፡ ነገም ለታሪካቸው ባዳ ሆኖ አገኙት፡፡ በአባባ መርዕድ ውሸት ታሪክ አልባ ሴት መሆናቸው ቆጫቸው፡፡ «ለሀገርሽ ምን ሠራሽ? ለትውልድ ምን አደረግሽ?» ብሎ ህሊናቸው ለጠየቃቸው ጥያቄ መልስ መመለስ እንዳለባቸው ያወቁት ቆይተው ነበር፡፡ ·ከስጦታዎች ሁሉ ውዱ ስጦታ ሀገርና ሕዝብን በታማኝነት ማገልገል ነው» የሚለው ሃሳብ ወደ አእምሯቸው መጣ፡፡ በቀሪ ዘመናቸው አንድ መልካም ተግባር በመፈጸም በአባባ መርዕድ እብለት የባከነ ታሪካቸውን ለመመለስ ቆርጠው ተነሱ፡፡ ሀገርና ሕዝብ ለማገልገል ጊዜው አሁን እንደሆነ ከመቼውም ጊዜ በላይ ተረዱ፡፡ በማስመሰል ትብታብ ተሸርበው ነበርና ካጎነበሱበት ቀና አሉ፡፡ የመጀመሪያ ተግባራቸው አባባ መርዕድን ማጋለጥ ይሆናል፤ ከዚያም በምኞት ሳይሆን በትጋት የሚያምን ትውልድ መፍጠር፡፡

«ሰው በእስተርጅና . . . ዋሽቶ ማስታረቅ ሲገባው እንዴት ዋሽቶ ያጣላል? አበስኩ ገበርኩ» እያሉ ወደ ቤታቸው ሄዱ፡፡

# ዓለም አቀፍ

## ዩናይትድ ኪንግደም የተዘረፉትን የጋና 'የአክሊል ጌጣጌጦች' በብድር ልትመልስ ነው

እንግሊዝ አንዳንድ የጋና "የአክሊል ጌጣጌጦችን" ከአሳንቴ ንጉሥ ፍርድ ቤት ከዘረፈቻቸው 150 ዓመታት በኋላ በብድር ለመመለስ ወስናለች። በረዥም ጊዜ የብድር ስምምነት ከሚመለሱት 32 ዕቃዎች መካከል የወርቅ ቱቦ አንዱ መሆኑን ተገልጿል።

የቪክቶሪያ እና አልበርት ሙዚየም (ቪ ኤንድ ኤ) 17 ቅርሶችን ሲያበድር 15ቱ ደግሞ ከብሪቲሽ ሙዚየም የሚሰጡ ናቸው። ከበርካታ ትውልዶች ቁጣ በኋላ “አዲስ የባሕል ትብብር ስሜት” እንደሚመጣ ተስፋ አደርጋለሁ ሲሉ የጋና ዋና ተደራዳሪ ገልጸዋል።

በዩናይትድ ኪንግደም ያሉ አንዳንድ ሙዚየሞች ክርክር ያለባቸውን ቅርሶች በቋሚነት እንዳይመልሱ በሕግ ተከልክለዋል። እንደዚህ ያሉ የብድር ስምምነቶች ቅርሶችን ወደ ሀገራቸው እንዲመለሱ ለማድረግ እንደ አማራጭ መንገድ ይወሰዳል። ቅርሶቹ ላይ የባለቤትነት ጥያቄ የሚያነሱ ሀገሮች ግን የብድር ስምምነቱ እንግሊዝ ቅርሶቹ ባለቤት እንደሆነች እንደተቀበሉ ለማመልከት ጥቅም ላይ ሊውል ይችላል ብለው ይፈራሉ።

የቪ ኤንድ ኤ ዳይሬክተር የሆኑት ትሪስትራም ሃንት የፍርድ ቤት ወርቅ ዕቃዎች "ከእኛ ዘውድ ጌጣጌጥ" ጋር እኩል ናቸው ሲሉ ለቢቢሲ ተናግረዋል። በብድር ከሚሰጡት አብዛኞዎቹ ቅርሶች የተወሰዱት በ19ኛው ክፍለ ዘመን በብሪታንያ እና በአሳንቴ ጦርነት ወቅት ነው። ሰይፍ እና የንጉሡን ነፍስ የማንጻት ኃላፊነት ባላቸው ባለሥልጣናት የሚለበሱ የወርቅ ኒሻኖች ይገኙባቸዋል።

ሃንት አክለውም ሙዚየሞች “በጦርነት እና



በወታደራዊ ዘመቻዎች የተዘረፉ ቅርሶችን በፍትሐዊነት እንዴት ማካፈል እንደምንችል የማሰብ ኃላፊነት አለብን” ብለዋል።"እንዲህ ዓይነት ሽርክና እና ልውውጥ ከፈጠርን ሙዚየሞቻችን የሚዘጉ አይመስለኝም።"

አዲሱ የባህል ሽርክና "በኋላ በር የመመለስ አይደለም" በማለት አጥብቀው ተናግረዋል። ይህም በቋሚነት ንብረቶቹን ለጋና የሚመልስበት መንገድ አይደለም ማለት ነው። የሦስት ዓመት የብድር ስምምነቶች (ለተጨማሪ ሦስት ዓመታት የማራዘም ዕድልም አለው) ከጋና መንግሥት ጋር የተደረገ ሳይሆን ከአሁኑ የአሳንቴ ንጉሥ አሳንቴሄን ዳግማዊ ኦቶምፎ ኦሴይ ቱቱ የተደረሰ ነው።

ግዛቱ አሁን የጋና የዘመናዊ ዴሞክራሲ አካል ቢሆንም አሳንቴሄኔ አሁንም ተደማጭነት ያለው ሥርዓት ነው። ቅርሶቹ የአሳንቴሄንን የብር ኢዮቤልዩ በሚከበርበት በአሳንቴ ክልል ዋና ከተማ ኩማሲ በሚገኘው በማኒሺያ ቤተመንግሥት ሙዚየም ለዕይታ ይቀርባሉ። የአሳንቴ የወርቅ ቅርሶች የአሳንቴ ንጉሣዊ መንግሥት ምልክት ሲሆኑ ከቀድሞው የአሳንቴ ነገሥታት መንፈስ ጋር የተሳሰሩ እንደሆነ ይታመናል።

ለጋናም ከቤኒን ብሮንዝ ጋር የሚወዳደር ጠቀሜታ አላቸው። ቤኒን ብሮንዞች በዘመናዊቷ ደቡብ ናይጄሪያ ውስጥ ከቤኒን ቤተ መንግሥት በብሪታንያ የተዘረፉ በሺዎች የሚቆጠሩ ቅርጻ ቅርጾች እና ሐውልቶች ናቸው። ናይጄሪያ እነዚህ ቅርሶች ወደ ሀገራቸው እንዲመለሱ ለአስርተ ዓመታት ስትጠይቅ ቆይታለች።

የጋና የባህል ሚኒስትር ልዩ አማካሪ ናና ኦፎሪያታ አዩም ለቢቢሲ እንደተናገሩት "ቅርሶች ብቻ ሳይሆኑ መንፈሳዊ ጠቀሜታም አላቸው:: የሀገሪቱ ነፍስ አካል ናቸው:: ወደ ራሳችን የምንመለስበት ቅርስ ነው::"ብድሩ በዘረፋው ዓመታዊ በዓል ላይ መሆኑ "ጥሩ መሠረት ከመሆን ባለፈ ለተፈጠረው ሁከት የፈውስ እና የመታሰቢያ ምልክት ነው" ሲሉ ተናግረዋል።

የዩናይትድ ኪንግደም ሙዚየሞች ከጋና የተወሰዱ በርካታ ቅርሶችን ይዘዋል። በጣም ዝነኛ ከሆኑት መካከል የአሳንቴ አካል ከሆኑት አንዱ የሆነውን በሰው ፊት ቅርጽ የተሠራው ወርቅ ይገኝበታል። አሳንቴዎች በአንድ ወቅት በምዕራብ አፍሪካ ከነበሩት ግዛቶች መካከል በጣም ኃይለኛ እና ጠንካራ ከሆኑት አንዱን ከመመስረት ባለፈ ወርቅ እና ጨርቃ ጨርቅ ንግድ ይሳተፉ እንደነበር ቢቢሲ ጠቅሶ ዘግቧል።

# ስፖርት





# የመጀመሪያው ታላቅ የወንጪ ሩጫ ነገ ይካሄዳል

**ብርሃን ፈይሳ**

የአሜሪካዎቹ ሆፐኪፕተን ስቴት ፓርክ፣ ግራንት ፓርክ እና ሴንትራል ፓርክ በዓለም አትሌቲክስ የፕላቲኒየም ደረጃ ከተሰጣቸው ስድስቱ ዋና ዋና የማራቶን ውድድሮች መካከል የሆኑት የቦስተን፣ ቺካጎ እና ኒውዮርክ ማራቶኖች የሚካሄዱባቸው ስፍራዎች ናቸው፡፡ ለንደንን የመሰሉ ትልልቅ ከተሞችም በፓርኮቻቸው ውስጥ የተለያዩ ስፖርታዊ ሁነቶችን ያስተናግዳሉ፡፡ በእርግጥ ነፋሻማ አየር ያላቸውና በውሃማ ስፍራዎች ዳርቻ የሚደረጉ ሩጫዎች በብዛት የተለመዱ ናቸው፡፡

በአትሌቲክስ ስፖርት የሚካሄዱ የጎዳና ሩጫዎች ጥንታዊ ስፍራዎችን፣ የተንጣለሉ ዘመናዊ ጎዳናዎችን እንዲሁም ለቱሪዝም መስህብነት የተገነቡ ፓርኮችን መሠረት አድርገው ይካሄዳሉ፡፡ ከ1990ዎቹ ወዲህ በዓለም አቀፍ ደረጃ በማደግ ላይ ካሉ ዘርፎች መካከል ስፖርትና ቱሪዝም ይጠቀሳሉ። ስፖርታዊ ውድድሮች ቱሪስቶችን የመሳብ ትልቅ አቅም እንዳላቸው ሁሉ የቱሪዝም ስፍራዎችም ስፖርታዊ ሁነቶችን ለማስተናገድ ተመራጭ ናቸው። በዓለም አቀፍ ደረጃ የሚካሄዱ ትልልቅና ዓመታዊ ውድድሮች ለዚህ ማሳያ ማድረግ ይቻላል፡፡ አዳዲስ የቱሪዝም ፕሮጀክቶችን ለጎብኚዎች ለማስተዋወቅም ሆነ ይበልጥ ሳቢ ለማድረግም ስፖርታዊ ሁነቶችን ማዘጋጀት አንደኛው መንገድ መሆኑንም የዘርፉ ባለሙያዎች ይጠቁማሉ፡፡

በኢትዮጵያም ይኸው ሁኔታ እየተለመደ የመጣ ሲሆን፤ በሀገር አቀፍ ደረጃ የተገነቡ የቱሪስት መስህቦችና ፓርኮች የስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራዎችንም ያካተቱ ናቸው፡፡ ለአብነት ያህል በአዲስ አበባ ከተማ የተገነቡት የወዳጅነት አደባባይ ቁጥር 1 እና 2፤ እንዲሁም




**የወንጪ ሩጫ ፡**

የእንጦጦ ፓርክ የጤና ቡድኖች እንዲሁም በግላቸው ስፖርት ለመሥራት የሚፈልጉ ሰዎች የሚመርጧቸው ስፍራዎች መሆናቸው ይታወቃል፡፡ ታላቁ የኢትዮጵያ ሩጫም በእንጦጦ ፓርክ ሳምንታዊ የሆነ የሩጫ ውድድር በተከታታይ ሲያካሂድ ቆይቷል፡፡

ነገ ደግሞ ሀገራዊ ከሆኑ የቱሪዝም ፕሮጀክቶች መካከል አንዱ በሆነው የወንጪ ደንዲ ኢኮ ቱሪዝም የ10 ኪሎ ሜትር  የሩጫ ውድድር እንደሚደረግ ታውቋል፡፡ በገበታ ለሀገር ፕሮጀክት የተገነባው ዓለም አቀፍ ደረጃ ያለው ይህ የቱሪስት መዳረሻ ከሳምንታት በፊት መመረቁን ተከትሎ በደንዲ ሐይቅ ዳርቻ ባህላዊ የፈረስ ግልቢያ እና የፈረስ ጉግስ ተካሂዷል፡፡

ፕሮጀክቱ ሲገነባ ልዩ ልዩ ዓለም አቀፋዊ ይዘት ያላቸው ስፖርታዊ፣ ባህላዊና ኪነጥበባዊ ሁነቶችን ማስተናገድ እንዲችል ታስቦ ሲሆን፤ የወንጪና ደንዲን ሐይቆች የሚያገናኝ 21 ኪሎ ሜትር (ዓለም አቀፍ ደረጃ ያለው የግማሽ ማራቶን) ትራክን አካቷል፡፡

በኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን፣ በኦሮሚያ ወጣቶችና ስፖርት ቢሮ ምዕራብና ደቡብ ምዕራብ ሸዋ ዞኖች፣ በኦሮሚያ ቱሪዝም ኮሚሽን እንዲሁም በወንጪና ደንዲ ኢኮ ቱሪዝም ፕሮጀክት አስተባባሪነት የሚደረገው ታላቁ የወንጪ ሩጫ ነገ ጥር 18/2016 ዓ.ም ለመጀመሪያ ጊዜ የሚካሄድ ሲሆን፤ በቀጣይነት በየዓመቱ የሚካሄድም ይሆናል። የቱሪዝም መዳረሻውን እንዲሁም ውድድሩን ለማስተዋወቅ ከኢትዮጵያውያን ባሻገር፤ የኬንያ እና ኡጋንዳ አትሌቶች በ10 ኪሎ ሜትር የጎዳና ሩጫው እንደሚሳተፉ ተረጋግጧል፡፡ የዓለም አትሌቲክስ ማኅበር ተወካዮችም በዚህ ውድድር ላይ እንዲታደሙ ግብዣ ተደርጎላቸዋል፡፡ በውድድሩ 2 ክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች እንዲሁም 22 ክለቦችና የማሰልጠኛ ተቋማት ይሳተፋሉ፡፡ 186 ወንድና 116 ሴት በጥቅሉ 302 አትሌቶች ሲሮጡ፤ በዓለምና ሀገር አቀፍ ውድድሮች ውጤታማ የሆኑ ታዋቂ አትሌቶች ተሳታፊዎች ናቸው፡፡ በዚህም በወንዶች በኩል ሞገስ ጥኡማይ፣ ጫሉ ዴሶ፣ ካሌብ ካሼቦ፣ ሰለሞን በሪሁ፣ ቢተው አደመ፣ ገመቹ ኢዳኦ፣ ሮባ መርጋሳ እና ሌሊሳ አራርሳን የመሳሰሉ ታዋቂ አትሌቶች ውድድሩን በጠንካራ ፉክክር እንዲታጀብ ያደርጋሉ በሚል ይጠበቃል፡፡

በሴቶች መካከል በሚካሄደው ውድድርም አሸቴ በከሪ፣ ትዕግስት ከተማ፣ ደራ ዲዳ፣ በቀለች ተኩ፣ ብዙሀገር አደራ፣ በቀለች ዳባ፣ ትዕግስት ጌትነት፣ መሰሉ በርሄ እና አዌ መገርሳን የመሳሰሉ አትሌቶች ለመሸናነፍ እርስ በእርሳቸው የሚያደርጉት ፉክክር ውድድሩን አጓጊ ያደርገዋል፡፡ ውድድሩ በሁሉም የዕድሜ ክልል የሚከናወን ሲሆን፤ አንጋፋ አትሌቶች እንዲሁም የሕፃናት 1 ኪሎ ሜትር ሩጫ ተዘጋጅቷል፡፡ በዚህም 33 አንጋፋ፤ እንዲሁም 300 ሕፃናት እንደሚገኙ መረጃዎች ያመላክታሉ፡፡ በውድድሩ አሸናፊ ለሚሆኑ አትሌቶች ከሜዳሊያ ባለፈ እስከ 10ኛ ባለው ደረጃ የሚያጠናቅቁ  የገንዘብ ሽልማትም ያገኛሉ፡፡ ለሽልማቱ ከ1 ሚሊየን ብር በላይ የተመደበ ሲሆን፤ አሸናፊ አትሌቶች 150ሺህ፣ ሁለተኛ የሚሆኑ 100ሺህ፤ እንዲሁም፣ በሦስተኛነት ደረጃ ለሚገቡ 70ሺህ ብር ይበረከትላቸዋል፡፡